# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 111 ታኅሣሥ 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## “ግብፅ የዓባይ ግድብን የውዝግብ ማዕከል የምታደርገው የውሃው ብቸኛ ባለቤት ለመሆን ካላት ፍላጎት ነው”

*ያዕቆብ አርሳኖ(ዶ/ር)*
*የውሃ ፖለቲካ ተመራማሪ*



**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ ግብፅ የዓባይ ግድብን በተደጋጋሚ የውዝግብ ማዕከል ለማድረግ የምታደርገው ጥረት የውሃው ብቸኛ ተጠቃሚ እና ባለቤት እኛ ነን ከሚል ፍላጎት የመነጨ መሆኑን የውሃ ፖለቲካ ተመራማሪው ያዕቆብ አርሳኖ(ዶ/ር)ተናገሩ።

የውሃ ፖለቲካ ተመራማሪው ያዕቆብ አርሳኖ(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ግብጽ በተደጋጋሚ የዓባይ ግድብን የውዝግብ ማዕከል ለማድረግ የምታደርገው ጥረት ዓባይን ጨምሮ በጠቅላላ በናይል ተፋሰስ ላይ በታሪክም በተፈጥሮም መብታችን ሊነካ አይችልም ከሚል መነሻ የሚመነጭ ነው ።

ግብፆች ከኢትዮጵያ ጋር የመደራደር ፍላጎት ካጡ ቆይተዋል የሚሉት ተመራማሪው የግብፆች ፍላጎት በተለይም የውሃውን ባለቤትነት ኢትዮጵያ እንድትለቅላቸው እንጂ ኢትዮጵያ ባለመብት መሆኗን እና የውሃው አመንጪ ሀገር እንደመሆኗ የራሷ የልማት ፍላጎት እንዳላት ጠፍቷቸው አይደለም ሲሉ ገልጸዋል ።

ግብፆች የሚሉት የውሃ ሙሉ ባለቤትነት ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች ውሃ አመንጪ ሀገራት ተቀባይነት እንደሌለው እንደሚረዱ ተናግረው በ 4ኛው ዙር የተደረገውን ድርድር እንዲሁም ከዛም በፊት በነበሩ

“ግብፅ የዓባይ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

## መንግሥት ለትግራይ ክልል የሰብዓዊ ርዳታ በበቂ መጠን እያቀረበ ነው

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ፕሮጀክቶቹን አጥፎ አስፈላጊውን በጀት መድቦ የሰብዓዊ ዕርዳታን ከሌሎች አካባቢዎች በተሻለ ብቻ ሳይሆን በበቂ መጠን ለትግራይ ክልል እያቀረበ እንደሚገኝ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገለጸ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ (ዶ/ር) በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ትናንት መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

ሚኒስትሩ በመግለጫቸው ከሰሞኑ በትግራይ ክልል የተከሰተው ድርቅና ረሃብ ከ77 ጋር የሚስተካከል ቀውስ ሊፈጥር ወደሚችልበት ደረጃ እየተሸጋገረ ነው በሚል የተሰጠው መግለጫ ፈጽሞ የተሳሳተ ነው፡፡ አጋር አካላት የርዳታ አቅርቦት ቢያቆሙም መንግሥት

መንግሥት ለትግራይ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## በመዲናዋ የምገባ አገልግሎት ከ779 ሺህ በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል

### - ለአገልግሎቱ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጓል

**አማን ረሺድ**

**አዲስ አበባ**፡- በመዲናዋ ከ779 ሺህ በላይ ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምገባ ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡ ለአገልግሎቱ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉንም ተገልጿል፡፡

የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተርና የግብዓት አቅርቦት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ምነወር ኑሪዲን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኤጀንሲው በአዲስ አበባና በዙሪያዋ በሚገኙ 629 ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ 779 ሺህ 231 ተማሪዎች የምገባ አገልግሎት እያቀረበ ይገኛል። በከተማዋ በሚገኙ ከቅድመ መደበኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚማሩ 779 ሺህ 231 ተማሪዎች

በመዲናዋ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



## ለአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ መስተንግዶ 161 ሆቴሎች ዝግጅት እያደረጉ ነው

ገጽ 5



















# የምክክሩን ሂደት ተደራሽ ማድረግ የመገናኛ ብዙኃንና የኪነጥበብ ባለሙያዎች የየዕለት ተግባር ሊሆን ይገባል

## - ለሀገራዊ ምክክሩ ከ60ሺህ በላይ ተሳታፊዎች ተለይተዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የሀገራዊ ምክክሩን ሂደት ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ የመገናኛ ብዙኃንና የኪነጥበብ ባለሙያዎች የዕለት ተዕለት ተግባር ሊሆን እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ ለሀገራዊ ምክክሩ የተሳታፊ ልየታ በተካሄደባቸው አካባቢዎች ከ60 ሺህ በላይ ተሳታፊዎች መለየታቸው ተጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን "ለሀገራዊ ምክክርና መግባባት የኪነጥበብ፣ የማስታወቂያና የሁነት ዝግጅት ተቋማትና ባለሙያዎች ሚና" በሚል መሪ ሀሳብ ከተቋማት ኃላፊዎች፣ ከጥበብ ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት ውይይት አካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ (ፕ/ሮ) በወቅቱ ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት፤ የሀገራዊ ምክክሩን ሂደት ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ የመገናኛ ብዙኃንና የኪነጥበብ ባለሙያዎች የዕለት ተዕለት ተግባር ሊሆን ይገባል፡፡

የምክክሩን ዓላማ ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ለማድረግ ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ተቀራርቦ መሥራት ሲቻል ነው ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ የኪነጥበብ፣ የማስታወቂያና የሁነት ዝግጅት ተቋማትና ባለሙያዎች የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

ምክክሩ የመንግሥትና የምሑራን ሀሳብ ብቻ የሚንጸባረቅበት ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያውያን በእኩል ተሳትፈውበት የጋራ ሀገራዊ መግባባት የሚፈጠርበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለምክክሩ መሳካት የመገናኛ ብዙኃንና የኪነጥበብ ባለሙያዎች ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ገልጸው፤ የምክክሩን


ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ
መስፍን አርዓያ (ፕ/ሮ)

ሂደት ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ የዕለት ተዕለት ተግባር ሊሆን እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

በኮሚሽኑ የሚዘጋጁትን ሁነቶችና በእራሳቸው አጀንዳ እየቀረጹ ስለምክክሩ ዓላማ ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ያደረጉ ተቋማትን አመስግነዋል። የሀገራዊ ምክክር ሂደቱ ተጠናቆ ዓላማውን እውን ማድረግ እስከሚቻል ድረስ መገናኛ ብዙኃን ለምክክሩ የሚሰጡትን ሽፋን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል።

ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ጀምሮ በተሠሩት ሥራዎች አማራና ትግራይ ክልሎችን ሳይጨምር በሌሎች አካባቢዎች ከ60 ሺህ በላይ ተሳታፊዎች ተለይተዋል ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ፤ በቀጣይ በክልልና በፌደራል ደረጃ ተገናኝተው አጀንዳ የሚሰበሰብበት ሁኔታ ይመቻቻል ብለዋል።

ምክክሩን አሳታፊና አካታች ለማድረግ በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በእስያና በሌሎች የውጭ ሀገራት ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር በበይነ መረብ አማካኝነት ውይይት ማድረጋቸውን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ብሌን ገብረመድኅን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል የተባባሪ አካላትን ለመለየት የአሠልጣኞች ሥልጠና የሚሰጡ የዩኒቨርሲቲ መምህራንን ከቀጣይ ሳምንት ጀምሮ ማሠልጠን እንደሚጀምሩ አመልክተዋል፡፡

በትግራይ ክልልም የተለያዩ ኅብረተሰቡን ሊወክሉ የሚችሉ የሲቪክ ማኅበራትን፣ የሴቶች ፎረም፣ የአካል ጉዳቶች ማኅበራት፣ የሀገር ሽማግሌዎችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ተገናኝተው መወያየታቸውን አስታውቀዋል፡፡

በሁለቱ ክልል የተሳታፊና የተባባሪ አካላት ልየታ ያልተጀመረው በክልሎች ባለው የሰላም ሁኔታና በቂ የሰው ኃይል ባለመኖሩ መሆኑን አውስተዋል፡፡

የተሳታፊና ተባባሪ አካላት ልየታ በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች በቅርቡ አጀንዳ ማሰባሰብ እንደሚጀመር አመልክተው፤ በሂደት ላይ የሚገኘውን ሀገራዊ ምክክር ስኬታማ ለማድረግ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በውይይት መድረኩ የሀገራዊ ምክክሩ ኮሚሽነሮች፣ አርቲስቶች፣ የማስታወቂያ ባለሙያዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተገኙ፤ ሲሆን፤ ተሳታፊዎች ሀገራዊ ምክክሩን በመደገፍ ስኬታማ ለማድረግ ሁሉም በሙያ ዘርፋቸው እገዛ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

# መንግሥት ከዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ የነዳጅ ድጎማ አድርጓል

## . አምስት ሺህ 786 ተሽከርካሪዎች ከድጎማ ተጠቃሚነት ታግደዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት ለሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች ከዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ የነዳጅ ድጎማ ማድረጉን ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ። በአምስት ወራት አምስት ሺህ 786 ተሽከርካሪዎች ከድጎማ ተጠቃሚነት መታገዳቸው ተመላክቷል፡፡

በትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ብሔራዊ የታለመለት ነዳጅ ድጎማ ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ሰልማን መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች የኑሮ ጫና ለማቃለል የታለመ ዓላማ ያለው የነዳጅ ድጎማ ከሐምሌ 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። በዚህም በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት ለሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተሽከርካሪዎች ከዘጠኝ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ የነዳጅ ድጓማ ተደርጓል፡፡

የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎችን በመለየት የነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው ያሉት ፕሮጀክት አስተባባሪው፤ በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት ብቻ ለታለመለት የነዳጅ ድጎማ ከዘጠኝ ነጥብ 82 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉን አስታውቀዋል፡፡

እንደ ሰልማን ገለጻ፣ በድጎማ ማስተግበሪያ ሥርዓቱ ውስጥ የድጎማ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከተመዘገቡ 241 ሺህ 035 ጠቅላላ ተሽከርካሪዎች ውስጥ እስከ ኅዳር 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ 198 ሺህ 771 የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ድጎማ እያገኙ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

በድጎማ ሥርዓቱ ከተመዘገቡት ተሽከርካሪዎች 82 በመቶ የሚሆኑት ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸው፤ በበጀት ዓመቱ አምስት ወራት የድጎማ ተጠቃሚ የሆኑ ተጨማሪ 21 ሺህ 677 ተሽከርካሪዎች መኖራቸውንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡



የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ተግባራዊ መደረግ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ኅዳር 30 ቀን 2016 ዓ.ም በክልል እና ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት መዋቅሮች ተለይተው በማስተግበሪያ ሥርዓቱ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች 241 ሺህ 35 መድረሳቸውን አመልክተው፤ በአምስት ወሩ 10 ሺህ 17 ተጨማሪ ተሽከርካሪዎች መመዝገባቸውን አስታውቀዋል፡፡

ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተሰጣቸውን የታለመለት የነዳጅ ድጎማ ለግል ጥቅማቸው የሚያውሉና በሕገወጥ መንገድ ሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ አምስት ወራት ብቻ አምስት ሺህ 786 ተሽከርካሪዎች ከድጎማ ተጠቃሚነት እንዲታገዱ መደረጋቸውን አስታውቀዋል፡፡

አራት ሺህ 500 ተሽከርካሪዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ሳይሰጡ የተጠቀሙትን ከዘጠኝ ነጥብ 76 ሚሊዮን ብር በላይ የድጎማ ገንዘብ በዕዳ መልኩ መልሰው እንዲከፍሉ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

ከጥቅምት 15 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ኅዳር 30 ቀን 2016 ዓ.ም በጠቅላላው 38 ሺህ 415 የሚደርሱ ተሽከርካሪዎች ከድጎማ ተጠቃሚነት እንዲታገዱ መደረጉን አስታውሰው፤ በታለመ ነዳጅ ድጎማ አሠራር መሠረት በሚመለከታቸው የትራንስፖርት መዋቅሮች ወደ ድጎማ ተጠቃሚነት እንዲመለሱ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን መሠረት በማድረግ ወደ ድጎማ ተጠቃሚነት እንዲመለሱ እየተደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ድጎማቸውን በአግባቡ ያልተጠቀሙ ተሽከርካሪዎች የድጎማ ተመላሽ ገቢ ማድረጊያ የቴሌ ብር አጭር ኮድ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ስም እንዲዘጋጅ ተደርጎ የድጎማ ተመላሽ በቴሌ ብር አጭር ኮድ ከኅዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እንዲጀመር ተደርጎ እየተሠራበት እንደሚገኝ አስታውሰዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ አምስት ወራት የታለመ ነዳጅ ድጎማ ተጠቃሚ ሆነው በማስተግበሪያ ሥርዓቱ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ከ46 ነጥብ 18 ቢሊዮን ብር በላይ በቴሌብር የነዳጅ ግብይት ተደርጓል ብለዋል፡፡




# የአብሮነት ቀን ‹‹አብሮነትን መኖር›› በሚል መሪ ቃል ታኅሣሥ 25 ይከበራል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የዘንድሮው የአብሮነት ቀን ታኅሣሥ 25 ቀን 2016 ዓ.ም «አብሮነትን መኖር» በሚል መሪ ቃል እንደሚከበር የበዓሉ አዘጋጅ ብሔራዊ ኮሚቴ አስታወቀ፡፡

ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በኢትዮጵያ ለ14ኛ ጊዜ የሚከበረው የአብሮነት ቀን ታኅሣሥ 25 ቀን 2016 ዓ.ም «አብሮነትን መኖር» በሚል መሪ ቃል በሳይንስ ሙዚየም ይከበራል፡፡

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህል፣ ማንነት፣ ቋንቋ እና እምነት ሀገር ናት ያለው ኮሚቴው፤ በዚህም የረጅም ጊዜ ታሪክና ጥንታዊ የሥልጣኔ ባለቤት የብዝኃ ባሕል መገለጫ ከሆኑት ጥቂት የዓለም ሀገራት አንዷ ናት፡፡ ይህንን ሀብትና ዕድል የበለጠ ለማጎልበት በብዝኃነትና በአብሮነት መካከል ያለውን ፋይዳዎች የማዳበርና የማጉላት ሥራ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትኩረት ተሰጥቶት እየተተገበረ ይገኛል ብሏል በመግለጫው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ26ኛ ጊዜ በሀገራችን ለ14ኛ ጊዜ የሚከበረውን ዓለም አቀፍ የአብሮነት ቀን መነሻ በማድረግ ከታኅሣሥ 20 እስከ ታኅሣሥ 25 ቀን 2016 ዓ.ም የአብሮነት ሳምንት ተብሎ በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ይከበራል፡፡

በዚህም መሠረት ታኅሣሥ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ‹አብሮነት በተግባር› በሚል በበጎ አድራጎት ሥራዎች እንደሚከበር የተጠቀሰ ሲሆን፤ በዕለቱ አቅመ ደካሞችን መንከባከብ የደም ልገሳን ጨምሮ ልዩ ልዩ የበጎ አድራጎት ተግባራት እንደሚከናወኑ ተገልጿል።

ታህሳስ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ደግሞ ‹አብሮነት በሚዲያ› በሚል አብሮነትን ለማጠናከር የሚያግዙ መልዕክቶች በመገናኛ ብዙኃን እንደሚተላለፍ የተጠቆመ ሲሆን፤ ታኅሣሥ 24 ስፖርትን ለአብሮነት በሚል ልዩ ልዩ ስፖርታዊ ክንውኖች ይካሄዳሉ፡፡ በዚህም በማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ ስፖርት ያለውን ሚና ለማጉላትና ስፖርትን ለአብሮነት ማጎልበቻ ለመጠቀም ዕለቱ በተለያዩ ስፖርታዊ ክንውኖች እንደሚከበር ኮሚቴው ገልጿል።

ሐሙስ ታኅሣሥ 25 ቀን 2016 ዓ.ም የፌዴራልና ከፍተኛ ሥራ ኃላፊዎች፣ የሀይማኖት አባቶችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በሳይንስ ሙዚየም መርሐ ግብር እንደሚካሄድ የጠቆመው ኮሚቴው፤ እለቱ በሁሉም አከባቢዎችም በድምቀት እንዲከበር እስከታች ባለው የመንግሥት አስተዳደርና የሃይማኖት ተቋማት ዝግጅት መደረጉንም አስታውቋል፡፡

ቀኑን በውጭ ሀገራት የሚገኙ የሀገሪቱ ዲፕሎማቶችና ዲያስፖራዎች ባሉበት ሆነው መላው ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ የሚያከብሩት ይሆናል፡፡

ፕሮግራሙ የነበረውንና ያለውን ሀገራዊ የሠላም ባሕልና የፖለቲካ ባሕላችን ለአብሮነታችን፤ ለሀገረመንግሥት ግንባታ ያለው ፋይዳ ላይ ሀገራዊ ንቅናቄና ግንዛቤ መፍጠር ያለመ ነው ያለው ኮሚቴው፤ በኅብረተሰቡ መካከል የመከባበር፣ መቻቻል፣ አብሮነት እና የሠላም ግንባታ አስተሳሰብ እንዲጎለብት የሚያስችሉ ተግባራት ይከናወናሉ ሲል አስታውቋል፡፡

ማኅበረሰቡ በመንግሥታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ የመሳተፍ ባሕል እንዲዳብር እና በመንግሥትና ሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክሩ ሥራዎች ይሠራሉ ብሏል ኮሚቴው በመግለጫው፡፡

ለበዓሉ መሳካት በባሕልና ስፖርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት የብሔራዊ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተዋቅረው አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉ የተገለጸ ሲሆን፤ መገናኛ ብዙኃን፣ ማኅበረሰቡና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በዓሉን ለማክበርና በብዝኃነት ውስጥ አብሮነትን የሚያጠናክሩ ተግባራት ላይ እንዲሳተፉ ኮሚቴው ጥሪውን አስተላልፏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ትውልዱ ችግሮችን በውይይት መፍታትን የብሩህ ዕጣ ፈንታው መሠረት አድርጎ ሊወስደው ይገባል!

ትላንትም ይሁን ዛሬ እንደሀገር ያጋጠሙንን ሆኑ አሁን ላይ እያጋጠሙን ያሉ ችግሮችን ተሻግረን ማለፍ ያልቻልነው ችግሮቹን ቁጭ ብለን በሰከነ መንፈስ መነጋገር ባለመቻላችን እንደሆነ ይታመናል። ለዚህም የመጣንበት የፖለቲካ አመለካከትና አመለካከቱ የወለደው የፖለቲካ ባሕል ዋነኛ ተጠቃሽ ነው።

በየትኛውም ማኅበረሰብ፤ በተለይ እንደኛ ባለ ብዝኃነት መገለጫው ፤ከዚያም በላይ የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪክ ባለቤት በሆነ ማኅበረሰብ ውስጥ፤ የሀሳብ ልዩነቶች መፈጠራቸው እንደ ችግር የሚቆጠር ሳይሆን፤ ለለውጥ መነቃቃት እንደ አንድ መልካም ዕድል የሚታይ ነው።

ይህን መልካም እድል መሸከም የሚችል የአስተሳሰብ መሠረት ማዋቀር አለመቻላችን፤ ረጅም ዘመናት ባልተገባ መልኩ በግጭት አዙሪት ውስጥ እንድንዳክር አድርጎናል። በዚህም በየዘመኑ የነበረው ትውልድ ከፍያለ ዋጋ ለመክፈል ተገድዷል። የታሪካችንም አብዛኛው ምዕራፍ የግጭትና የጦርነት ሆኗል።

ከዚህ የተነሳም በአንድ ወቅት ከነበርንበት ትልቅነት /የሥልጣኔ ማማነት/ ቁልቁል ወርደን አሁን የምንገኝበት አንገት የሚያስደፋ ድህነትና ኋላቀርነት ውስጥ እንድንገኝ ሆነናል። ድህነት እና ኋላቀርነት ለሚፈጥረው ለማኝነት/ ጠባቂነት/፤ ለማኝነት ለሚፈጥረው የልብ ስብራት ሰለባ ለመሆን ተገደናል።

የቀደሙት አባቶቻችን እስከዛሬ ዓለምን እያስደመሙ ያሉበትን እውቀትና ክህሎት በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ትንሳዔ እያገኘ ዘመኑን በሚዋጅ የዕድገት ምዕራፍ ውስጥ አድጎ ሀገርን እንደቀደሙት ዘመናት የትልቅነት ማማ ማድረስ የምንችልበት ሰላምና መረጋጋት አጥተን ዘመናት አስቆጥረናል።

ከራሳችን ጋር መታረቅ አቅቶን ሰላምና መረጋጋት ባጣንባቸው ረጅም ዓመታት፤ ዓለም ከሁሉም በላይ ለሰላሙ ትኩረት ሰጥቶ፤ የሰላሙ ፍሬ/በረከት የሆነውን ዕድገትና ብልጽግና እያጣጣመ ነው፤ ከዕለት ተለት የሕይወት ፈተና ወጥቶ ሕይወትን ድንቅ እያደረገ ይገኛል ።

እኛ እንደ ሀገር ትናንቶቻችንን በአግባቡ አውቀን ከነሱ ለመማር የተከፈተ ልብና አእምሮ በማጣታችን፤ በተመሳሳይ ስህተት አዙሪት ውስጥ እንድንገኝ፤ ተመሳሳይ ያልተጋባ ዋጋ እንድንከፍል እያደረገን ነው። ከዚህም ባለፈ ነገዎቻችን የጽልመት ግርዶሽ እንዲሸፍናቸው ጫና እየፈጠረ ነው ።

አሁን ላይ እውነታዎች እየተቀየሩ፤ ትውልዱ ከትናንት ስህተቶች ተምሮ ዛሬውንም ሆነ ነገዎችን ብሩህ ለማድረግ በሚያስችል መነቃቃት ውስጥ ለመገኘቱ ተስፋ ሰጭ ተግባራት እየታዩ ነው። ለዚህ ደግሞ ችግሮችን በመወያየት ለመፍታት እያሳየ ያለው አሁነኛ መነቃቃት ተጠቃሽ ነው ።

ትውልዱ እያሳየ ያለው ይህ ችግሮችን በውይይት የመፍታት መነቃቃት በአንድም ይሁን በሌላ ትላንቶችን እና ትናንቶች የተገዙበትን እሳቤ ከመረዳት፤ እሳቤው የቱን ያህል ሀገርና ሕዝብን ዋጋ እንዳስከፈለና እያስከፈለ እንዳለ ከመገንዘብ የመነጨ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት አይከብድም ።

በርግጥ አውቀነውም ይሁን ሳናውቀው፤ አስተውለነው ይሁን ሳናስተውለው ብዙ የኪሳራ ዘመናትን ኖረናል። ለዘመናት ኪሳራ የዳረገን ልዩነቶቻችንን በኃይል እና በሴራ የመፍታት የጥፋት መንገድ፤ አሁን ላይ አንድ ርምጃ ሊያስኬደን አይችልም። ከዚህ ይልቅ እንደ ሀገር በብዙ ውጣ ውረድ የገነባነውን ብሔራዊ ማንነት ሊያፈርስና ሊበትነን የሚችል አሁናዊ የስጋት ምንጭ ነው።

ይህንን አሁናዊ ስጋት አስተማማኝ በሆነ መንገድ መሻገር የምንችለው፤ ችግሮቻችንን በውይይት ለመፍታት በትውልዱ ውስጥ ለተፈጠረው መነቃቃት ፤ተገቢውን ዕውቅና ስንሰጥና ፤እንደ ትውልድ ብዙ ትውልዶችን ዋጋ እያስከፈለ ካለው የግጭት አዙሪት መውጣት ስንችል ብቻ ነው ።

በኃይልና በሴራ እርሾ እየተቦካ ሲጋገር የኖረው የሀገራችን የፖለቲካ አስተሳብ /ሥርዓት ትውልዶችን በየዘመኑ ከአስከፈለው ያልተገባ ዋጋ አንጻር ፤ በዚህ ትውልድ እየታየ ያለው አዲስ የፖለቲካ እሳቤ ፤ እሳቤው የወለደው መነቃቃት፤ እንደሀገር ከፊታችን የካሳ ዘመን መቅረቡን አመላካች ነው።

አሁን ላይ በችግሮቻችንን ዙሪያ በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብለን ለመነጋገር የደረስንበት መግባባት ፤ይህን ተከትሎም ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ማቋቋማችንና ወደሥራ መግባቱ ፤ ትውልዱ ከትናንት ስህተቶች መማር ስለመጀመሩ፤ ችግሮችን በውይይት የመፍታት አዲስ ሀገራዊ የአስተሳሰብ ለውጥ ስለመምጣቱ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ይህ የአስተሳሰብ ለውጥ ሙሉ በሙሉ ህይወት ዘርቶ ለረጅም ዘመናት ያጣናቸውን ባለብዙ ተስፋ ቀናቶች ነገ ላይ በተሻለ መልኩ እጃችን ለማስገባት፤ በዚህም ሀገራችንን እንደሀገር ወደቀደመችበት የዕድገትና የስልጣኔ ማማ ለመመለስ ትውልዱ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የጀመረውን ሀገራዊ እሳቤ የራሱ፤ የብሩህ ዕጣ ፈንታው መሠረት አድርጎ ሊወስደው ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ያልተጠቀምንበት ሀገር በቀል ዕውቀት

በምስጋና ፍቅሩ

አንድ ማኅበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ ተፈጥሮን መሠረት አድርጎ የረጅም ዓመታት ልምዱን ታሳቢ በማድረግ የሚያካብተው እውቀት ‹‹ሀገር በቀል ዕውቀት›› ይባላል። ሀገር በቀል እውቀት አንድ ማኅበረሰብ ከተፈጥሮና ከአካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ባለው ቁርኝት የሚያገኘውን፣ የሚያዳብረውንና የእለት ተእለት ሕይወቱን ወይም መስተጋብሩን የሚያሳልጥበት እውቀት ነው፡፡

እውቀቱ ለብዙ ማኅበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንደመፍትሔ ሆኖ የሚያገለግል፤ አንድ ማኅበረሰብ በዘመናት ሂደት ውስጥ እንደ ማኅበረሰብ ያጋጠሙትን/የሚያጋጥሙትን ግለሰባዊም ሆነ ማኅበራዊ ተግዳሮቶችን ተሻግሮ አሁን ላይ እንዲገኝ ትልቅ አበርክቶ ያለው ነው።

ይህ እውቀት መገለጫው ብዙ ነው፤ ለምሳሌ ዛሬ ድረስ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት አርሶ አደሩ የሚያርሠው መሬት ላይ ምን መዝራት እንዳለበት፣ እንዴት እንደሚዘራ፣ የመሬቱን ለምነት ለመጠበቅ የሚያደርጋቸው ተግባራት፣ የአካባቢው የአየር ንብረት ሁኔታ ምን እንደሚመስል እና ምን መደረግ እንዳለበት የሚያውቀው ከትውልድ ትውልድ ሲወራረድ በመጣ ሀገር በቀል እውቀቱ ነው፡፡

ሀገር በቀል ዕውቀት በመጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀዳሚ ከሆኑ ሀገራት መካከል ጃፓን፣ ሩሲያ፣ ቻይና እና ታይላንድ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ ሀገራት ያሏቸውን ሀገር በቀል እውቀቶች ወደ ዘመናዊ መንገድ በመቀየር እንዲሁም በቀላሉ ሌሎች ሊጠቀሙባቸው በሚቻልበት መንገድ በመለወጥ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎችም መትረፍ የቻሉም ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገር በቀል ዕውቀት ጠቀሜታ ላይ ግንዛቤን በመፍጠር ረገድ መሻሻሎች እየታዩ ይገኛሉ፡፡ ሀገር በቀል እውቀትን በተመለከተ ከዚህ ቀደም በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ያልነበረ ሲሆን፤ ዛሬ ላይ ግን በአዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ውስጥ ተካቶ ተማሪዎች እንዲያውቁት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃም ትኩረት ተሰጥቶት ጥናት እና ምርምሮችን ከማድረግ ባሻገር መረጃዎችን አሰባስቦ ለመሰነድ ጅምር ሥራዎች መኖራቸው እየተነገረ ነው። ሁኔታው የዘገየ ቢሆንም ዓለም ለሀገር በቀል እውቀቶች ትኩረት ሰጥቶ በስፋት እየተንቀሳቀሰ ባለበት በዚህ ጊዜ እንደ ሀገር በጉዳዩ ዙሪያ ከተኛንበት ነቅተን መገኘታችን የሚበረታታ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህም ባለፈ የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ዕውቀት በትምህርት ደረጃ ለሁሉም ማኅበረሰብ ተደራሽ እንዲሆን ዓላማ ያደረገው ‹‹የኢትዮጵያ ሀገር በቀል ዕውቀት ማዕከል›› መመሥረቱ እንደ ጅምር የሚታይና ብዙ አስቦ መሥራትን የሚጠይቅ የቤት ሥራ ቢሆንም ይበል እና ይጠንክር የሚያሰኝ ተግባር ነው፡፡

በተለይም ሀገር በቀል የባሕል መድኃኒቶችን በዘመናዊ መልክ ቀይሮ በሳይንሳዊ መንገድ በመታገዝ ለብዙኃኑ እንዲዳረስ ከማድረግ አኳያ ያለው ክፍተት በእጅጉ ከፍ ያለና ልዩ ትኩረት የሚሻ ነው። በችግሩ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያስረዱት፤ አንድም ለመድኃኒት የሚወጣውን የውጪ ምንዛሪ ከመቆጠብ፤ ሌላም የሐክምናውን ዘርፍ በሚገባ ከመደገፍ አንፃር ጠቀሜታው የጎላ ነው ፡፡

ሀገር በቀል የሆኑ የፖለቲካና የኢኮኖሚ እውቀቶች ዘመኑን በሚዋጅ መንገድ አጥንተን በዘርፉ ለሚያጋጥሙ ችግሮቻችን የመፍትሔ አካል አለማድረጋችን ሌላው ችግራችን እንደሆነ የሚስማሙ ጥቂት አይደሉም። እነዚህን ዕውቀቶች መርምሮና አዳብሮ ዘመኑን በዋጀ መልኩ ከመጠቀም አኳያ በርካታ ክፍተቶች እንዳሉም ይስማማሉ፡፡

አዲሱ ትውልድ የውጪውን ዓለም ይናፍቃል፤ ለሌላ ሀገር ባሕሎች ተገዢ ሆኗል፤ ተብሎም ይታማል፡፡ ነገር ግን የራሱን ሀገር በቀል እውቀትና ጥበብ የሚያስተምረውና የሚያሸጋግርለት አንድ ወጥ ሥርዓት አለመዘርጋቱ ለእንዲህ አይነት አመለካከት ዳርጎት እንደሆነስ፡፡ ያ ባይሆን ለሌላ ሀገር ባሕል እጁን ለመስጠት አይገደድም፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ የታሪክ ምሑሩ ፍቅሬ ቶሎሳ(ፕ/ር) በአንድ ወቅት፤ ‹‹ሀገር በቀል ዕውቀቶቻችንን ባለመጠቀማችን፣ ባለማሳደጋችን ብሎም ለትውልድ እንዲተላለፉ ባለማድረጋችን የውጭ ተፅዕኖ ውስጥ እንድንወድቅና ውስጣዊ ማንነታችን እንዲወሰድብን በር ከፍቷል›› ብለዋል፡፡

> **‹‹ሀገር በቀል እውቀት ጥቅም ላይ ይዋል›› ሲባል የሌላ ሀገር ዕውቀት ወደ ሀገር ቤት አይግባ ማለታችን አይደለም። ከሌሎች የምናገኛቸው ጠቃሚ እውቀቶችንም በአግባቡ ከራሳችን እውቀት ጋር አጣጥመንና አቀናጅተን ብንጠቀምባቸው ችግሮቻችንን ልንፈታባቸው እንችላለን**

እንደ ሀገርም ይሁን እንደ ግለሰብ ብዙ ነገሮችን በሰነድ መልክ ማዘጋጀት (ሰንዶ) ማስቀመጥ ላይ ብዙ ክፍተቶች መኖራቸው አይካድም፡፡ ሀገር በቀል ዕውቀቶቻችንን ለመጪው ትውልድ ተደራሽ ለማድረግ በሚገባ ሰንዶ የማስቀመጡ ጉዳይ ከወሬ በዘለለ በተግባር ብዙ ርቀት አልተሄደበትም፡፡

ከሀገር በቀል ዕውቀቶቻንን መካከል ባሕላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶቻችን ሌላው ያልተጠቀምንባቸው ሀብቶቻችን ናቸው፡፡ በሀገራችን እንደየአካባቢው ባሕልና ወግ የተለያዩ ስኬታማ የግጭት አፈታት ባሕላዊ ሥርዓቶች አሉ። እነዚህን አቅሞች በመጠቀም እዚህም፤ እዚያም የሚታየውን ግጭት ለመፍታት በሚገባው ልክ ትኩረት ሰጥተን አልሠራንም፡፡

እዚህ ላይ መርሳት የሌለብን ጉዳይ፤ ‹‹ሀገር በቀል እውቀት ጥቅም ላይ ይዋል›› ሲባል የሌላ ሀገር ዕውቀት ወደ ሀገር ቤት አይግባ ማለታችን አይደለም። ከሌሎች የምናገኛቸው ጠቃሚ እውቀቶችንም በአግባቡ ከራሳችን እውቀት ጋር አጣጥመንና አቀናጅተን ብንጠቀምባቸው ችግሮቻችንን ልንፈታባቸው እንችላለን፡፡

ያለንበት ወቅት በሰኮንዶች ውስጥ ዓለምን ለማማተር የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉበት ከመሆኑ አንጻር ብዙ አማራጮችን ተጠቅመን መረጃዎችን ልናገኝ እንችላለን፡፡ ይሁንና ከውጭ የሚገኙ እውቀቶችን እንደ ወረዱ ማኅበረሰቡ ላይ ለመጫን መሞከር ኪሳራ ሊኖረውም ይችላል። በጤና፣ በማኅበራዊ መስተጋብር፣ በትውልዶች የስብዕና ግንባታ ላይም የሚፈጥረው ተጽዕኖ ሊኖር እንደሚችል መገንዘብም ተገቢ ነው። ስለሆነም ወደ ሀገራችን የምናስገባቸው የዓለም ተሞክሮዎችና እውቀቶች ከማኅበረሰቡ ባሕል፣ ሃይማኖትና ሞራል ጋር እንዳይጋጩ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ቀደም ስለ ግብረገብ፣ እፅዋት ጥበቃና እንክብካቤ፣ ጥንታዊ ስዕሎች አሳሳል፣ ቀለማት አቀማመም፣ ወዘተ ትምህርቶችን በመስጠት ትውልዱ አባቶቹ ለዘመናት ያቆዩትን እውቀት እንዲወርስ ሲሠራ ነበር፡፡ እውቀቶቹ ለሀገሪቱ የቀደሙ እድገቶች መሠረትም ነበሩ፡፡ ዛሬም አስፈላጊው ትኩረት ከተሰጣቸው ለእድገትና ለሥልጣኔ የመኖራቸው አበርክቶ ቀላል አይሆንም፡፡

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሀገር በመሆኗ የብዙ ባሕል፣ ቋንቋ እና እሴቶች ባለቤት መሆን ችላለች፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን በብዙ ባሕሎች ውስጥ ያሉ ሀገር በቀል እውቀቶችን ጠብቆ ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ባለመቻሉ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን እንዳታገኝ ሆናለች፡፡

ሀገር በቀል ዕውቀቶች ከመጠበቅ፤ ከማስተዋወቅ እና አግባብ ባለው መልኩ ከመጠቀም አንጻር የሚመለከታቸው አካላት በተለይም የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በባሕል ላይ የሚሠሩ ተቋማትና ምሑራን እንዲሁም መገናኛ ብዙኃን በትኩረት ሊሠሩ ይገባል፤ በኪነ ሕንፃ፣ በፍትሕ ሥርዓት፣ በፊደል ቀረፃ እና በሌሎች ተግባራት ቀዳሚ የነበረች ሀገር ዛሬ እዚህ መድረሷ ቁጭት ውስጥ ሊከተን ይገባል፡፡ ይህ ቁጭት በሚፈጥረው መነቃቃት ሀገራችንን ከፍ ለሚያደርጉ ሀገር በቀል እውቀቶች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተን መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል፤ ይህን ለማድረግ አልረፈደም፡፡

ዜና



የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፉአድ ኪያር

# የንግድና ኢንቨስትመንት ክርክሮች በፍጥነት እልባት መስጠት ይገባል

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የንግድ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ችሎቶችን በማጠናከር ለንግድና ኢንቨስትመንት ክርክሮች በፍጥነት እልባት መስጠት እንደሚገባ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፉአድ ኪያር አስታወቁ።

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በንግድ ውዝግብ አፈታት ላይ ያተኮረ ውይይት ትናንት አካሂደዋል።

በውይይቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፉአድ ኪያር እንደገለጹት፣ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ የንግድ ክርክሮችን የሚመለከት ራሱን የቻለ የንግድ ክርክር ችሎት በ2015 ዓ.ም ከፍቷል። ይህም የንግድ ጉዳዮች በፍጥነት እልባት እንዲያገኙ ይረዳል። ይህም ክርክሮች የተሳለጡ፣ ጥራት ያላቸውና የንግዱ ማኅበረሰብ ጊዜውን ፍርድ ቤት እንዳያጠፋ ያግዛል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት በጉዳይ አይነት በማደራጀት የንግድ፣ የባንክ፣ ኢንሹራንስና የኮንስትራክሽን ክርክሮች የሚታዩበት ችሎት ነው። ይህም የንግድ ጉዳዮች በፍጥነት እልባት እንዲያገኙ አድርጓል።

አንድ ሀገር ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ መሆኗ ከሚለዩበት መንገድ አንዱ ራሱን የቻለ የንግድና ኢንቨስትመንት ችሎት መኖሩ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የንግድ ችግሮች ሲገጥሙ የሚታይበት ልዩ ችሎት መኖሩ ኢንቨስተርን ለመሳብ እንደሚረዳም ገልጸዋል።

ራሱን የቻለ የንግድ ክርክር ችሎት መኖሩ ኢትዮጵያ ለንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ መሆኗን ያሳያል ያሉት አቶ ፉዓድ፤ የንግድ ጉዳዮች ላይ ክርክሮች ሲያጋጥሙ ወጪንና ጊዜን በሚቆጥብ ሁኔታ እልባት ለመስጠት ይረዳል። ጠንካራ የንግድና ኢንቨስትመንት ችሎት በማደራጀት ኢንቨስትመንት በመሳብ ረገድ ትልቅ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ተቋም ዳይሬክተር አቶ ዮሐንስ ወልደገብርኤል በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የንግድ ክርክር ጉዳዮችን ለማሳለጥ ከፍርድ ቤቶችና ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀራርቦ መሥራት አስፈላጊ ነው። የግልግል ዳኝነት የሚሰጥባቸው የንግድ ጉዳዮች በመሆናቸው ከመደበኛ የንግድ ችሎቱ ጋር በጋራ በመሥራት ኢትዮጵያን ለኢንቨስትመንት ምቹ ማድረግ ይገባል።

የመጨረሻውን የፍትሕ ሥራ የመሥራት ኃላፊነት የመንግሥት ነው ያሉት አቶ ዮሐንስ፤ በሀገራችን ከፍርድ ቤት ውጭ የግልግል ዳኝነት የሚያከናውኑ ተቋማት ብዙ ናቸው፤ መንግሥትም በሕግ ፈቅዷል ብለዋል።

መደበኛ ፍርድ ቤቶች ከመደበኛ ውጪ የዳኝነት ሥራ ከሚሠሩ የግልግል ተቋሞች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር የንግድና ኢንቨስትመንት ክርክሮችን በአጠረ ጊዜ መፍታት እንደሚገባ አመልክተው፤ በብዛት ወደ ንግድ ምክር ቤቱ የሚቀርቡ የመንግሥትና የዓለም አቀፍ ድርጅት ጉዳዮች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰብ ነጋዴዎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

# ለአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ መስተንግዶ 161 ሆቴሎች ዝግጅት እያደረጉ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- ለ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ የሚሳተፉ እንግዶችን ለመቀበል 161 ሆቴሎች ተመርጠው ዝግጅት እያደረጉ መሆኑ ተገለጸ።

በቱሪዝም ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ዩኒት አስተባባሪ አቶ ቴዎድሮስ ደርበው በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ በመጪው ጥር ወር መጨረሻ ላይ በአዲስ አበባ ለሚካሄደው 37ኛው የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስተባባሪነት የሚመለከታቸው አካላት ያቀፈ ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ተዋቅሯል። ከእነዚህም መካከል እንግዶቹ የተሳካ ቆይታ እንዲኖራቸው የቱሪዝም ሚኒስቴር የራሱን ድርሻ ወስዶ እየሠራ ይገኛል። በዚህም ለአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ መስተንግዶ 161 ሆቴሎች ዝግጅት እያደረጉ ነው።

በጉባኤው በርካታ ቁጥር ያላቸው የአፍሪካ ሀገራት መሪዎችና የተለያዩ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች ተሳታፊ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል ያሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ እነዚህ እንግዶች የሚስተናገዱባቸው ሆቴሎችና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሀገርን ስም በመልካም ሊያስጠሩና የሀገርን ገጽታ የሚገነባ መልኩ ጥራት ያለው አገልግሎት ሊያቀርቡ ይገባል ብለዋል።

የሆቴል አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶችም የእንግዶቹን ደህንነት በተጠበቀ መልኩ በኢትዮጵያዊ ጨዋነትና እንግዳ አቀባበል ማስተናገድ እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ ሆቴሎች ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት በመስጠት የጉባኤው ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ በሚኖራቸው ቆይታ ጥሩ ትዝታ እንዲኖራቸው የማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው ገልጸዋል።



ይህንን ለማሳካትም ተሳታፊዎቹን ያስተናግዳሉ ከተባሉ ባለ ኮከብ ሆቴሎች ሥራ አስኪያጆች ጋር መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት መካሄዱን አውስተው፤ በውይይቱም ሆቴሎች ለሚከፈላቸው ገንዘብ ተመጣጣኝ አገልግሎት እንዲያቀርቡ፣ አላግባብ ዋጋ እንዳይጨምሩ፣ ከጤናና ከድንገተኛ አደጋ ጋር በተያያዘ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ከስምምነት መደረሱን ጠቅሰዋል።

በቀጣይም በከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ሆቴሎቹ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን በአካል በመገኘት ጉብኝት የሚደረግ መሆኑን ጠቁመው፤ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩልም ከኤሌክትሪክ ኃይል፤ ውሃና ቴሌኮም አገልግሎት ጋር በተያያዘ ችግር የሚገጥም ከሆነ በወቅቱ ለመፍታት ክትትልና ድጋፍ የሚደረግላቸው መሆኑን ተናግረዋል።

# ግብፅ የዓባይ ግድብን የውዝግብ ማዕከል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሂደቶች ግብፆች አልተስማማንም የሚሉት እኛ የምንፈልገው ካልሆነ ሌሎችን ቢጠቅምም ባይጠቅምም ድርድሩ ይፈርሳል ከሚል ግምት መሆኑን ተናግረዋል።

የውሃ ተመራማሪው እንደሚሉት ሱዳንና ግብፅ ውሃውን ሙሉ ለሙሉ የመጠቀም ስምምነት ስላላቸው ስምምነቱን ኢትዮጵያም ሌሎች ሀገራትም እንዲያፀድቁ ይፈልጋሉ። ነገር ግን ኢትዮጵያ በሉዓላዊ ግዛቷ ውስጥ የውሃ ሀብቷን ለዜጎቿ የማልማት መብት ያላት መሆኑን መገንዘብ ይገባል። የዓባይ ግድብ ሥራ እየተጠናቀቀ በመሆኑ ሌሎች ግድቦችም በዓባይ ምንጮች ላይ መሠራት አለባቸው።

ኢትዮጵያ ውስጥ በውሃ ሀብቶች ላይ የሚሠሩ ልማቶች የታችኞቹን ተፋሰስ ሀገራት እስካልጎዱ ድረስ መቀጠል እንዳለባቸው ተናግረው በዓባይ ግድብ ላይም እነዚህ ሀገራት እንዳይጎዱ እና ለጋራ ተጠቃሚነት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረጉን አስታውሰዋል።

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ ግብፆች መልማት የኢትዮጵያ መብት መሆኑን ተቀብለው ሲመጡ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ድርድር ማካሄድ ይቻላል። ሆኖም ድርድሩ እንዲሳካ የግብፆች ሀሳብ መለወጥን ይጠይቃል። በኢትዮጵያ በኩል ግን ምንጊዜም ለድርድር ክፍት ተደርጓል።

በቀጣይ ውሃን በጋራ የመጠቀምና የመልማት ጉዳይ ላይ ብዙ ሀሳቦች ቀርበው በድርድር ወደ ጋራ ልማት ሊያመራ ይችላል ያሉት ዶክተር ያዕቆብ ይህ ካልሆነ ግን ጊዜ የሚወስድ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።

ግብፅ በሚዲያ የምታደርገው ስም የማጥፋት ዘመቻ ትክክል እንዳልሆነ የተናገሩት የውሃ ተመራማሪው በኢትዮጵያ በኩልም የግል እና የመንግሥትም የሚዲያ ተቋማት፣ የማኅበራዊ ሚዲያ አንቂዎችና ተመራማሪዎች እንዲሁም የልማት ተቋማት የዓባይ ግድብ የኢትዮጵያ የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጉዳይ መሆኑን በማስረዳት ረገድ የሚደረገው እንቅስቃሴ መጨመር እንዳለበት ገልጸዋል።

# መንግሥት ለትግራይ ክልል የሰብዓዊ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ፕሮጀክቶቹን አጥፎ አስፈላጊውን በጀት መድቦ የሰብዓዊ ርዳታን ከሌሎች አካባቢዎች በተሻለ ብቻ ሳይሆን በበቂ መጠን ለትግራይ ክልል እያቀረበ እንደሚገኝም አብራርተዋል።

"የሰብዓዊ ርዳታ አቅርቦትና ፖለቲካ መቀላቀል የለባቸውም" ያሉት ሚኒስትሩ፤ እንዲህ ያለ ቀውስ ሲኖር ማወጅ ያለበት የፌዴራል መንግሥቱ የአደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት መሆኑን እና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ተገምግሞ የሚደርስበት እንጂ ፖለቲካና ሰብዓዊ ጉዳይን በማያያዝ የሚወሰን እንዳልሆነ ነው የገለጹት።

የአደጋ ስጋት አመራር ምክር ቤት በትግራይ ክልል በአራት ዞኖች ድርቅ መከሰቱን ቢያረጋግጥም ከ77 ድርቅና የረሃብ ቀውስ ጋር ሊስተካከል ይችላል የሚል ማረጋገጫ እስካሁን አለማውጣቱንም ጠቅሰዋል።

ሕዝብን ቀጣይነት ወዳለው የልማት ሥራ ከማስገባት ይልቅ በግምገማ ስም ለወራት ተሰባስቦ የሚቀመጥ አመራር፤ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ባለሙያ በታጣቂ ስም በአንድ ቦታ ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በተመደበ በጀት እየቀለበ በምን ሞራል ስለትግራይ ሕዝብ መናገር ይችላል ሲሉም ጠይቀዋል።

በሕዝብ ሽፋን የሚደረግ የትኛውም አይነት ፕሮፖጋንዳ ተቀባይነት እንደሌለው የገለጹት ሚኒስትሩ፤ የትግራይ ክልልን ጨምሮ በአማራ ክልል ስምንት ዞኖች፣ በአፋር ክልል ሦስት ዞኖች እና በሌሎች ክልሎች በሚገኙ አካባቢዎች 3 ነጥብ 8 ሚሊዮን ወገኖች የድርቅ አደጋ እንዳጋጠማቸው ጠቅሰዋል።

መንግሥት ፕሮጀክቶቹን አጥፎ አስፈላጊውን በጀት መድቦ የሰብዓዊ ርዳታን ከሌሎች አካባቢዎች በተሻለ ብቻ ሳይሆን በበቂ መጠን ለትግራይ ክልል እያቀረበ ነው ብለዋል።

መንግሥት ካለፈው ሐምሌ ወር ጀምሮ በሦስት ዙር አንድ ሚሊዮን 725 ሺህ ኩንታል የርዳታ እህል በድርቅና በጎርፍ ወደ ተጠቁ አካባቢዎች እያሰራጨ እንደሚገኝ ገልጸው፤ የአጋር አካላትን ጨምሮ እየተደረገ ያለው ድጋፍ በገንዘብ ሲተመን 15 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር የሚደርስ መሆኑን ተናግረዋል።

በመግለጫቸው፤ በአማራ ክልል የሠላም ጥሪ በማወጅ ሠላምን ለማስጠበቅ መንግሥት በሠራው ሥራ በርካታ መሣሪያ የታጠቁ ቡድኑ አባላት ጥሪውን ተቀብለው ወደ ተሐድሶ ሥልጠና መግባታቸውን ጠቅሰው፤ "መንግሥት የሠላም በሮችን አሁንም ክፍት እንዳደረገ ይገኛል" ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በተዛባ የፕሮፖጋንዳ ቅስቀሳ ተደናግረው ወደ ሁከትና ብጥብጥ ገብተው የነበሩ በሺዎች የሚቆጠሩ ታጣቂዎች ወደ ተዘጋጀላቸው የተሐድሶ ማዕከላት እየገቡ ይገኛሉ። ወደ ተሐድሶ ማዕከላት ከገቡት መካከል ሁለት ሺህ 500 ያህሉ የቡድን መሣሪያ የታጠቁና አመራሮች ናቸው። ከሠላም ጥሪው በፊት ከአምስት ሺህ 500 በላይ ከጉዳዩ ጋር ንክኪ ያላቸው አካላት በፀጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ሥር የዋሉና እጅ የሰጡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ወደ አራት ሺህ የሚጠጉት የተሐድሶ ሥልጠና ወስደው ወደ ኅብረተሰቡ ተቀላቅለዋል።

ለሰው ሕይወት መጥፋትና ለንብረት መውደም ተጠያቂ የሚሆኑ 360 ግለሰቦች ተለይተው ጉዳያቸው በሕግ እንዲታይ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፣ 288 የሚሆኑት ግለሰቦች ደግሞ ጉዳያቸው በደረቅ ወንጀል የሚታይ ይሆናል ብለዋል።

ከፕሪቶሪያው ስምምነት በኋላ በጋምቤላና በቤኒሻንጉል ክልሎች በተደረጉ ውይይቶች ነፍጥ ያነሱ ኃይሎች ወደ ሠላም እንዲመጡ በመደረጉ በአካባቢዎቹ ከመቼውም ጊዜ ሠላም መስፈኑን ጠቁመው፣ በአንጻሩ መንግሥት በተደጋጋሚ የሚያደርገውን የሰላም ጥሪ ወደ ጎን ብለው የሕዝብን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች በመጻረርና ሃብትና ንብረትን በማውደም ተግባር ላይ በተሰማሩ አካላት ላይ ርምጃ መውሰድ መቀጠሉን ገልጸዋል።

መንግሥት ከሸኔ ጋር የሠላም ንግግር ለማድረግ መሞከሩን ያወሱት ሚኒስትሩ፤ ሆኖም ጥረቱ ባለመሳካቱ ሠላምን ለማስጠበቅ ሲባል በሸበር ቡድኑ ላይ ርምጃ እየተወሰደ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

አሁን ላይ በሀገሪቱ አንጻራዊ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ መቻሉን ገልጸው፣ በቀጣይም መላው ሕዝብ ከፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር ሠላምን ለመጠበቅ እና ለማጽናት የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፍ ጥሪ አቅርበዋል።

# በመዲናዋ የምገባ አገልግሎት ከ779 ሺህ በላይ ተማሪዎች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በቀን ሁለት ጊዜ የምገባ አገልግሎት ተጠቃሚ ሁነዋል።

የምገባ አገልግሎቱ በዋናነት ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ተገኝተው በአግባቡ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያስችላል ያሉት አቶ ምነወር፤ በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ወላጆች እፎይታ የሰጠ አገልግሎት በመሆኑ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

የምገባ አገልግሎት በሚሰጠባቸው ትምህርት ቤቶች በቂ የመመገቢያ አዳራሽ፣ የግብዓት ማስቀመጫና የማብሰያ ክፍሎች መኖራቸውን የገለጹት ኃላፊው፤ ጥራቱን የጠበቀና የተመጣጠነ ምግብ ለተማሪዎች በመቅረብ ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

ከተማ አስተዳደሩ በትምህርት ዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች ለመፍታት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለአገልግሎቱ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉን አስታውቀዋል።

ከምገባ አገልግሎቱ ጋር በተያያዘ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን ገልጸው፤ በቀጣይ የተማሪዎች ምገባን በዘላቂነት በማስቀጠል በኢኮኖሚ አቅም ማነስ ከትምህርት ገበታ የሚርቁ ተማሪዎችን ችግር ለመፍታት በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

ኤጀንሲው የሚሰጠው የምገባ አገልግሎት ተማሪዎችን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ከምገባ ባለፍ የደብተርና የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦትና የተማሪዎች ደንብ ልብስ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን አቶ ምነወር አስረድተዋል።

ለምገባ አገልግሎቱ መሳካት ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሚና በተጠናከረ መንገድ እንዲወጡ አቶ ምነወር ጥሪ አቅርበዋል።

# ኢትዮጵያዊነት በባቡል ኸይር

ስምስም መንግሥቱ

ከሥፍራው የደረስነው ረፋድ ላይ ነበር። ከበር ላይ እንግዶችን የሚቀበሉ የድርጅቱ ሠራተኞች ተቀበሉን። ወደ ውስጥ ዘለቅን። አንዳንዶች ስማቸው እየታየና በድርጅቱ የተሰጣቸውን መታወቂያ እያሳዩ ወደ አዳራሽ ውስጥ ገቡ። እነዚህ እንግዶች ሳይሆኑ የድርጅቱ ቋሚ ተጠቃሚ መሆናቸው በድርጅቱ ሠራተኞች እየተረጋገጠ ወደ ውስጥ እንዲገቡ ተደረገ።

እኛ በድርጅቱ የሚሠሩ ሥራዎችን እንድንጎበኝ ተፈቅዶልን ጉብኝታችንን ከአዳራሽ ጀመርን። በአዳራሹ ውስጥ አረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች፣ ህፃናት የያዙ እናቶች፣ ጎልማሶች፣ ወጣቶች ሁሉም አይነት የህብረተሰብ ክፍሎች ነበሩ።

የሰዎቹ እዛ መኖር ምክንያቱን ላልተረዳ ሰው፤ ስብሰባ ተጠርተው ሊመስል ይችላል። የቆሸሸ ልብስ የለበሰ አለመኖሩም ችግረኞች ናቸው ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል። በአንድ አዳራሽ ውስጥ የተሰባሰቡት ሰዎች ቆሸሾ መታየት የድህነት መገለጫ መሆን የለበትም የሚለውን የድርጅቱን መመሪያ አክብረው እንጂ፤ የተሰበሰቡት ድርጅቱ ቋጥሮ የሚሰጣቸውን የዕለት ጉርሳቸውን የሚጠባበቁ ሰዎች ነበሩ ።

በተለያየ ምክንያት ለችግር ተጋልጠው ሌማታቸው ባዶ ሆኖ እጃቸውን ቢዘረጉም ንጽህናቸውን ግን መጠበቅ እንዳለባቸው በማስገንዘብ ድርጅቱ ንጽህናቸውንም እንዲጠብቁ ሳሙና በመስጠት ያበረታታቸዋል። ልብስ ለሌላቸውም ከበጎ አድራጊዎች የተገኘ ልብስ እንደሚሰጣቸው በጉብኝታችን ወቅት ተነግሮናል።

የምግብ እደላ መርሃግብሩ ከስድስት ሰአት በኋላ ነበር። በአስጎብኚያችን እንደተነገረን እነርሱ ግን ከረፋድ ጀምሮ በአዳራሹ ተገናኝተው የግል ጨዋታቸውን እየተጫወቱ መጠበቅ ልማዳቸው አድርገውታል። እኛም ቀድመን ተገኝተን ስለነበር እውነታውን አረጋግጠናል። አንዳንዶቹ ቀድመው የሚገኙት መድኃኒት ለመውሰድ፣ ልብስ የቸገራቸው ድጋፍ ለመጠየቅ፣ ሌላም ጥያቄ ያላቸው ለድርጅቱ ጥያቄያቸውን ለማቅረብ ነው። ሠራተኞች በበኩላቸው በማስተናገድ ፋታ አልነበራቸውም።

በማብሰያ ቤት ክፍል ውስጥ የነበሩ ሴቶችም ምሣ ለማድረስ እየተረባረቡ ነበር። ወጥና እንጀራው ተዘጋጅቶ፤ ከማብሰያው ጎን ምግብ የሚታሰርበት ሳህን ተሠናድቶ ነበር። ሳህኖቹ ምግቡን የሚቀበሉ ሰዎች ቢሆንም፤ ምግብ የሚቋጠርላቸው የምሣ ዕቃው በድርጅቱ ሠራተኞች ተሰብስቦ እና ታጥቦ የሚቀርብ ነው።

የእንጀራ መጋገሪያ ክፍሉም በአንድ ጊዜ ብዙ እንጀራ ለመጋገር የሚያስችል ምጣድ የተዘጋጀበት ነው። ድርጅቱ የሚሠራውን ሥራ ለማየትም ሆነ ለመደገፍ ፍላጎት ያለው እንጀራ ይጋግራል። አንድ እንጀራ ጋግሮ 50 ብር ይለግሳል። ዓላማው ድጋፍ በመሆኑ ወንዶችም እንዲሳተፉ ይደረጋል። ሰዎች እንዲህ በቀላሉ ሠብዓዊ በጎ ተግባር በመፈጸም የዜግነት ግዴታቸውን ይወጣሉ። እኛም ተሳታፊ በመሆን ሌሎችን ተጋርተናል።

ድርጅቱ ዋና ዓላማና ግቡ የእለት ጉርስ ለሌላቸው ወገኖች ምሣና እራት በሳምንት አንድ ቀን ደግሞ ቁርስ በማብላት በጎ ተልእኮ መወጣት ቢሆንም፤ ጎን ለጎን በአልባሳት ስፌት፣ በጫማ ሥራ፣ በዳቦና እና በዳቦ ቆሎ የአጫጭር ጊዜ ሥልጠና በመስጠት የሙያ ክህሎት ይሰጣል። ይህን ዕድል እንዲያገኙ እያደረገ ያለውም በተለያየ ምክንያት ችግር ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ነው። በድርጅቱ ውስጥ በተለያየ የሥራ ዘርፍ ተቀጥረው የሚሠሩትም አብዛኞቹ እንዲሁ ሥራ ያልነበራቸው በችግር ውስጥ የነበሩ ናቸው።

ድርጅቱ እንዲህ ያሉ ዜጎችን እየረዳ ያለው ከአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ጋር በመተባበር ነው። መረዳት ያለባቸው ሰዎች ሳይረዱ እንዳይቀሩ ከሚኖሩበት ቀበሌ ማረጋገጫ መያዝ ይኖርባቸዋል። እኛ በአካል ተገኝተን ያየናቸውን እንጂ በጤና



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

ወይዘሮ ሐናን መሐመድ

እና በእድሜ ምክንያት ቤት ውስጥ ውለው አስታዋሽ የሌላቸውንም ድርጅቱ ቤት ለቤት እየረዳቸው እንደሆነም ከድርጅቱ ብቻ ሳይሆን ከሠራተኞችም ሰምተናል። እጅግ አቅም ላጡ ጥቂት ሰዎችም ቤት ተከራይቶላቸዋል። በጦርነት ምክንያት ተሰደው ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ሶሪያውያንም ወርሃዊ ቀለብ ይሰጣቸዋል።

እንዲህ ኃይማኖት እና ዘር ሳይለይ ለበጎ ተግባር የቆመና የተጎዱ ኢትዮጵያውያንን በመደገፍ ላይ የሚገኘው ድርጅት በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር፤ በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ በከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ሳይቀር ሥራው መታየቱን በፎቶ በማዕከሉ ውስጥ ይገኛል። በተለያየ ጊዜ ለማዕከሉ የተበረከተ የምስክር ወረቀትና ሽልማትም እንዲሁ አይተናል። ይህ ማዕከል በቡልኸይር የበጎ አድራጎት የምገባ ማዕከል ነው። በቡልኸይር የበጎ ሥራ በር ማለት ነው። ይህን ማዕከል አቋቁመው የበጎ ሥራ እየሠሩ ያሉት ወይዘሮ ሐናን መሐመድ ናቸው።

ወይዘሮ ሐናን አንቱታን የሚያሰጣቸው በጎ ሥራ እየሠሩ በመሆናቸው እንጂ በእድሜ ለአንቱታ አልበቁም። እኛም ሥራቸውን አክበረን አንቱ በማለት ስለበጎ ተግባራቸው፣ ስለራሳቸውም እንዲያጫውቱን ቆይታ አድርገናል። ወይዘሮ ሐናን ለበጎ ተግባር የተነሳሱበትን አጋጣሚ እንዲህ ያስታውሳሉ፤ በአንድ አጋጣሚ ፤ የትምህርት ቤት የደንብ ልብስ የለበሱ ሁለት ሴት ታዳጊዎች መገኘት ከሌለባቸው አካባቢ ሲወጡ በድንገት ይመለከቷቸዋል። አንዷ ፀጉሯን የተሸፋፈነች ሙስሊም ስትሆን፣ ሌላኛዋ ደግሞ በአንገቷ መስቀል ያደረገች ክር ያሰረች ክርስቲያን ናት። ልጆቹ የነበሩት ጎረምሶች በበዙበት ሥፍራ ነበር።

እርሳቸውም እናት ናቸውና ታዳጊዎቹ ለጥቃት በሚጋለጡበት ቦታ መገኘታቸው በጣም አሳሰቧቸው ነበር። ተናደውባቸዋልም። የነበሩበት ቤት ምግብ ቤት ቢሆንም በእነርሱ እድሜ የሚገኙበት ስፍራ ባለመሆኑ ማለፍ አልፈለጉም። ሲወጡ ጠብቀው ለምን እዛ ቦታ እንደተገኙ ጠየቋቸው። ታዳጊዎቹም እውነታውን ሊነግሯቸው አልፈለጉም ነበር። እርሳቸው ግን እውነቱን ካልነገሯቸው ተከትለዋቸው ቤተሰባቸው ጋር እንደሚሄዱና ያዩትንም እንደሚነግሯቸው ጠንከር ብለው ጠየቋቸው።

ከታዳጊዎቹ ያገኙት እውነታ ግን እርሳቸው እንዳሰቡት አልነበረም። ከቤታቸው ሲወጡ ውሃ ብቻ ጠጥተው እንደወጡ ምንም እንዳልቀመሱ ነገሯቸው። ምግብ ቤት የገቡት የሚበላ ፈልገው እንደሆነ ሲነግሯቸው ወይዘሮ ሐናን እንባቸውን ሊቆጣጠሩ አልቻሉም። ስሜታቸው ተነካ። ‹‹አላህ እድሜ ከሰጠኸኝ ሰዎች በእኩልነት በፍትህ ያለምንም ጫና የሚመገቡበት ማዕከል እከፍታለሁ። ›› ብዬ ለራሴ ቃል ገባሁ ይላሉ። ይህ ታሪክ የዛሬ አስር አመት ቢሆንም ለእኛም ታሪኩን ሲያጫውቱን ስሜቱ አሁን ላይም እንዳለቀቃቸው እያስታወሱ ሲያለቅሱ ነበር።

‹‹ሰዎችን የምንረዳቸው በተሳሳተ መንገድ ነው ። ሁሌም ፈራጆች ነን። እነዛን ልጆች ባልጠይቃቸው ኖሮ ችግራቸውን አልረዳም ነበር›› የሚሉት ወይዘሮ ሐናን፤ የታዳጊዎቹን የቤተሰብ ሁኔታ ባዩ ጊዜ ልባቸው በጣም እንደተነካ ነበር የገለጹልን። ‹‹እኛ ስለምንለብሰው ልብስና ስለምንይዘው ቦርሳ ስንጨነቅ፤ እነርሱ ለቀን ጉርስ ይጨነቃሉ። እኩል ፍጥረት፣ የአንድ ሀገር ዜጎች ሆነን አንዱ የሚርበው፣ ሌላው በተሻለ ሁኔታ የሚኖር መሆኑ እጅግ ያሳዝናል›› አሉ። ያሉባቸውን ችግሮች ከተገነዘቡ በኋላ ወይዘሮ ሐናን ወዳጆቻቸውን በማስተባበር ታዳጊዎቹ ለትምህርት ቤት የሚያስፈልጓቸውን ወጪ በማሟላት፣ ቤተሰቡም የእለት ጉርስ የሚያገኝበትን ምቹ ሁኔታ ፈጠሩላቸው።

የተለያየ ዝግጅት እያዘጋጁ ከጓደኛና ቤተሰብ ጋር በደስታ ማሳለፍ የተለመደ ነው። እርሳቸው ግን እንዲህ ያለው መሰባሰብ በበጎ ተግባር ላይም ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል የሚል እምነት ነበራቸው። ታዳጊዎቹን መነሻ አድርገው ጓደኞቻቸውን፣ ወዳጆቻቸውንና ቤተሰባቸውን በማስተባበር 70 ተማሪዎች እንዲታገዙ አድርገዋል። ወይዘሮ ሐናን በተለይም የተጎዱ ሴቶችን ማለፍ አይሆንላቸውም። ስለተጎዱ ሴቶች ሲያነሱም እምባ ይቀድማቸዋል። ይህ በጎ ሥራቸው እየሰፋ የምገባ ማዕከል እስከማቋቋም ደረጃ ደረሰ።

ወይዘሮ ሐናን አቅማቸው በቻለው ሰብዓዊ ተግባር ለመፈጸምና የዜግነታቸውን ድርሻ ለመወጣት እንጂ፤ ሕጋዊ የሆነ ተቋም አቋቁመው ለመንቀሳቀስ ሃሳቡ አልነበራቸውም። የሚረዷቸው ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ፤ አንዳንድ ሰዎችም ማዕከል እንዲያቋቁሙ ምክር ሲሰጧቸው፣ ሕጋዊ ማድረጉን መረጡ። ከጓደኞቻቸውና ወዳጆቻቸው ጋር በየወሩ ተገናኝተው የሚያሳልፉት ጊዜም ይህን ያህል ቁምነገር ያለው ሆኖ አልታያቸውም። ቁምነገር ላይ የሚውል ሥራ መሥራት እንደሚፈልጉ ነገሯቸው።

እነርሱም በሃሳባቸው ተስማምተው የድጋፍ ሥራውን በጋራ አጠናከሩት። በሂደትም ባቡልኸይር የበጎ አድራጎት ድርጅት የምገባ ማዕከል ሕጋዊ ሆኖ መሥመር የያዘው። ከተመሠረተም አምስተኛ ዓመቱን ይዟል። አሠራሩም ሕጋዊ እንዲሆን ማዕከሉ ከሚገኝበት አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ጋር እየተናበቡ መሥራት ጀመሩ። ከወረዳ ከሚመጣላቸው መረጃ በተጨማሪ ድርጅቱም የራሱን የማጣራት ሥራ ይሠራል። በዚህ መሠረት መረዳት ያለባቸው ሰዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

ማዕከሉ አገልግሎቱን መስጠት የጀመረው በኪራይ ቤት ውስጥ ሆኖ ነው። በወቅቱም ይረዳቸው የነበሩ ሰዎች 126 ብቻ ነበሩ። የበጎ ሥራቸውን የተገነዘበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሥሪያ ቦታ ፈቅዶላቸው በቦታው ላይ ግንባታ አከናውነው አሁን ላይ በተሻለ ሁኔታ አገልግሎቱን እየሰጡ እንደሆነ ነው ወይዘሮ ሐናን የነገሩን።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለሥልጣን ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ የአልባሳት እገዛ አድርገውላቸው እንደነበርና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የማዕከሉን ሥራ እንደሚያውቁ አጫወቱን። በአሁኑ ጊዜ በማዕከሉ የሚጠቀመው 3 ሺህ 880 አባወራ ነው። ምግቡ የሚቋጠርላቸው እንደቤተሰባቸው ብዛት ነው። አገልግሎቱን እየሰጡ የሚገኙት በቤተሰብ ደረጃ እስከ 15 ሰው በመታደግ ነው። በምገባ ማዕከሉ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል አርቲስቶችን ጨምሮ ከሀገር መሪዎች ጋር ሳይቀር ትልቅ ሥራ የሰሩ የሀገር ባለውለታዎች ይገኙበታል። እነዚህ ሰዎች ተሳቅቀው ችግራቸውን ደብቀው የቆዩ ናቸው። መታየትም አይፈልጉም።

የበጎ ሥራውን ለማየት የሚፈልግ ወይም ‹‹ልዘይራችሁ›› የሚል ካለ፤ ምን ይዘህ የሚል ጥያቄ ይቀርብለታል። ተረጂዎቹ የምግብ ብቻ ሳይሆን፤ የህክምናና ሌሎች ተጨማሪ ድጋፎችን የሚፈልጉ በመሆናቸው የሌሎች ድጋፍ ወሳኝ ነው። በጤና አገልግሎት የጤና መድህን ተገዝቶላቸው የሚጠቀሙ አሉ።

የኑሮ ውድነቱ ከሚሠሩት በጎ ሥራ ጋር እንዴት እየተወጡት እንደሆነም ወይዘሮ ሐናንን

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ኢትዮጵያዊነት በባቡል...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ጠይቀናቸው፤ ‹‹እኔ አንድ ደካማ ሰው ነኝ። ግን አላህ እየረዳኝ ነው።›› በማለት በአጭሩ መለሱልኝ። በየእለቱ ምግብ የሚቋጠርላቸው ብቻ ሳይሆኑ፤ 150 የሚሆኑት ቋሚ ሠራተኞቻቸው ሁኔታም ያሳስባቸዋል። እጅ ቢያጥራቸው እርሳቸውን ተስፋ አድርገው ጠዋት ለሥራ ወደ ማዕከሉ የሚመጡና የዕለት ምግባቸውን የሚቀበሉ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲያስቡ ይጨነቃሉ።

ለሠራተኞች ደመወዝ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ያወጣሉ። ይህ ሁሉ የበጎ ሥራ በቋሚ በጀት ሳይሆን፤ ከሀገር ውስጥም ከውጭም ለጋሾች እየታገዙ ነው። ለጋሾች በአይነትም በገንዘብ እንደአቅማቸውና እንደፍላጎታቸው እገዛ ያደርጋሉ። ከውጭ በአሜሪካን ሀገር ውስጥ የሚያስተባብሩ ለጋሾችን ማግኘት ችለዋል።

ሰዎች የሚያስተባብራቸው ካገኙ ለበጎ ፈቃድ ልባቸው ክፍት እንደሆነ በሥራቸው አጋጣሚ ትምህርትም እንዳገኙበት ነግረውናል። እርሳቸውም ሳይታክቱ የማስተባበሩን ሥራ ይሠራሉ። በማህበር የተደራጁ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታይ የሆኑ ወጣቶች፣ተማሪዎች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከጎናቸው እንደሆኑም ገልጸውልናል።

በማዕከሉ ድጋፍ እየተደረገላቸው ያሉትም ሆኑ ተቀጥረው የሚሠሩት እንዲሁም በተለያየ መንገድ ድጋፍ የሚያደርጉትና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡት ኢትዮጵያውያን ናቸው። ወይዘሮ ሐናን፤ ‹‹ለእኔ አንድ ኢትዮጵያዊም ሆነ ኬንያዊ ወይንም የሌላ ዜጋ አንድ ነው። በዘር፣ በኃይማኖት ልዩነት መፍጠር በፈጣሪም የማይደገፍ ከሰውም የሚጠበቅ አይደለም። በማዕከሉ ማን ቸገረው እንጂ ሃይማኖቱ እና ብሔሩ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ አይነሳም።›› ይላሉ። ማዕከሉ በተወሰነ ሰው ኃላፊነት ብቻ የሚከናወን እንዳልሆነ ለሀገር የተከፈተ መሆኑም ግንዛቤ እንዲያዝ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተካተቱበት አባላት ያለው ኮሚቴ ተዋቅሮ ሥራው እንደሚሠራ የነገሩን ወይዘሮ ሐናን፤ ፍትሐዊነት እንዲኖርና እርሳቸውም ችግር ቢያጋጥማቸው ሥራው ቀጣይ እንዲሆን ከማሰብ እንደሆነም ገልጸውልናል።

ወይዘሮ ሐናን ሰዎችን ያለልዩነት በሠብዓዊነት መርዳት፣ማገዝ ከቤተሰብም የወረሱት ሳይሆን አይቀርም። ስለቤተሰባቸው እንዳጫወቱን በመስጠት መልካምነትን የሚሠራ ቤተሰብ ነው ያላቸው። የእርሳቸውም መልካምነት ከቤተሰብ የመጣ ይሆን ብለን ጠይቀናቸው ‹‹ወላሂ እኔ አላውቅም›› በማለት የተጎዳን ማገዝ መርዳት የመንፈስ እርካታ እንደሚሰጣቸው ነው የገለጹልን።

ለጋስ በመሆን እናታቸውን ፣ ሴትና ወንድ አያታቸውን ያነሳሉ። ሠብዓዊነት ምን ማለት እንደሆነ ሳይገባቸው እናታቸው ወይዘሮ አበራሽ ዓሊ የበዛ ደግነት ሲያደርጉ እንደአባካኝ ያይዋቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። የሴት አያታቸው ደግነት ደግሞ ይገርማቸዋል። እርሳቸው እንደሚሉት ከውጭም ከሀገር ውስጥም በተለያየ መንገድ ስጦታ ስለሚበረከትላቸው በቤተሰቡ እድለኛ ተድርገው ይታያሉ። የተሰጣቸውን ስጦታ ግን እርሳቸው ሳይጠቀሙበት የሚሰጡት ለሌሎች ነበር። ይህን ያየው ቤተሰብ ግን በመቆጨት እራሳቸው እንዲጠቀሙበት ይደብቅባቸዋል።

አያታቸው ግን የለበሱትን ልብስ አውልቀው ከመለገስ ወደ ኋላ አላሉም። አንድ ቀን አንዲት ወደቤታቸው የመጣች ሴት ልብሷ ተቀዳዶ በማየታቸው የለበሱትን አውልቀው አለበሷት። መስጠት የለመደ እጅን መከልከል ወይም የመስጠት ሱስን ማስጣል እንደማይቻል አያታቸውን በምሳሌ ያነሳሉ።

ወንድ አያታቸውም በአካባቢያቸው ለመቃብርና ለተለያየ አገልግሎት የሚውል የግል መሬታቸውን በመስጠት ይታወቃሉ። በታሪክም ይታወሳሉ። ከአዲስ አበባ ከተማ 80 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሸኖ የሚኖሩት አያታቸው በአካባቢው የእህል ወፍጮ፣ ወፍጮቤት ውስጥ ለእህል ማበጠሪያ የሚውል ዘመናዊ ማበጠሪያ እንዲሁም ሬዲዮ፣ መኪና ያስገቡ፣ ፎቅቤት የሰሩ፣ የመጀመሪያው ሰው ናቸው። በወቅቱም የአካባቢው ማህበረሰብ በአድናቆት ያያቸው እንደነበርና በተለይም ሬዲዮን በሰሙ ጊዜ ‹‹ሐጂ ዓሊ ብሎ ሼጣን አመጣ›› ብሏቸውም ነበር። መኪናውንም ወደ አካባቢው ይዘው በገቡ ጊዜ የአካባቢው ነዋሪ በፈረስ ሆኖ በዘፈን አጅቧቸዋል።

አያታቸው ሀጂ አሊ ግብይት በደረሰኝ እንዲፈጸም በማድረግ፣ የሸኖ ቅቤንም ለውጭ ገበያ በማቅረብ በተለይም የተነጠረ ቅቤ የመን ለገበያ የላኩና የአረቡ ማህበረሰብ የሸኖን ቅቤ እንዲያውቅ በማድረግ ረገድ ከአካባቢው ቀዳሚ ሰው ናቸው። እነዚህ ሁሉ በአካባቢው ላይ እውቅናን አትርፎላቸዋል።

> **በዘር፣ በኃይማኖት ልዩነት መፍጠር በፈጣሪም የማይደገፍ ከሰውም የሚጠበቅ አይደለም። በማዕከሉ ማን ቸገረው እንጂ ሃይማኖቱ እና ብሔሩ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ አይነሳም**

ከዚህ ቤተሰብ የተገኙት ወይዘሮ ሐናን የተወለዱት ሸኖ ነው። ያደጉት ግን አዲስ አበባ ከተማ መሳለሚያ አካባቢ ከሚኖሩ ሴት አያታቸው ጋር ነው። አብረዋቸው እንዲሆኑ የተደረገው አያታቸው ጋር ሴት ልጅ ባለመኖሩ ምክንያት ነበር። ግን ሸኖ ወላጆቻቸው ጋርም ይመላለሱ ስለነበር በማሳደግ በኩል የወላጆቻቸውም ድርሻ እንዳለበት ይናገራሉ።

ወይዘሮ ሐናንን ስለትምህርታቸውም ጠይቀናቸው። 12ኛ ክፍል እንዳጠናቀቁ በግላቸው ባህሬን ሀገር ሄደው ‹‹እስላሚክ ፍትህ›› ተምረው ከባህሬን ዲስከቨሪ እስላም ፍትህ በዲፕሎማ ተመርቀዋል። አንድ ሰው ፍታዊ ሊሆን የሚያስችለውን ትምህርት ተከታትለዋል።

በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኝ እናት ሜዲካል ኮሌጅ ‹‹ቻይልድ ሳይኮሎጂ›› የሚባለውን የትምህርት አይነት ተምረዋል። በውጭም በሀገር ውስጥም የተማሯቸውን የትምህርት አይነቶች በጥሩ ውጤት ማጠናቀቃቸውንና ተሸላሚ እንደነበሩም አጫውተውናል። ወይዘሮ ሐናን ቻይልድ ሳይኮሎጂ የትምህርት ዘርፍ የመረጡበት ምክንያት ነበራቸው፤ ለሥራ አጋጣሚ ዱባይ ከተማ በነበሩበት ወቅት በከተማዋ ከተለያየ ዓለም የመጡ የሚማሩበት ትልቅ ትምህርት ቤት ነበር።

በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ አንዲት ኢትዮጵያዊት ልጇን ታስተምራለች። ተማሪዎችን ከበር ላይ የሚቀበሉ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች የሌላ ሀገር ዜጎችን አቅፈው ሲቀበሏቸው፤ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎቹን ግን በእጃቸው ብቻ ይጨብጧቸው ነበር። ልዩነት መፍጠራቸው ለወይዘሮ ሐናን ጥሩ ስሜት አልሰጣቸውም። ቁጭትም ፈጥሮባቸዋል። ቁጭቱ የተፈጠረው ኢትዮጵያዊቷ እዛ ትምህርት ቤት ውስጥ ልጆችዋን ማስተማር የቻለችው አቅሟ ቢፈቅድ ነው እና ክብሩም እኩል መሆን አለበት ከሚል ነበር።

ከተጎዱ ሰዎች ጎን መቆም ባህሪያቸው እንደሆነ የሚናገሩት ወይዘሮ ሐናን፤ በዛ ሀገር ያዩትን ልዩነት ለማስቀረት፣ በሌላ በኩልም ዱባይ ከተማ ውስጥ ትምህርት ቤት ከፍተው ኢትዮጵያውያንም መሥራት እንደሚችሉ በማሳየት ቁጭታቸውን ለመወጣት አቅደው ቻይልድ ሳይኮሎጂ ተማሩ።

ወይዘሮ ሐናን በዱባይ ከተማ አሜሪካኖች፣ እንግሊዞች፣ ህንዶች የተለያዩ ዜጎች ትምህርት ቤት ከፍተው ስለሚያስተምሩ እርሳቸውም አንዱ ኢትዮጵያዊ ለመሆን የነበራቸውን እቅድ አላሳኩም። አንዱ ምክንያት ትዳር መመስረታቸው ነው። አምስት ልጆች በተከታታይ ወለዱ። ሌሎችም ምክንያቶች ተደማምረው አልተሳካላቸውም።

ያደኩት በሥራ ነው የሚሉት ወይዘሮ ሐናን፤ ከቤተሰብ ጋር በንግድ ሥራ ውስጥ በመቆየታቸው አሁንም በንግድ ሥራ ላይ ይገኛሉ። ወይዘሮ ሐናን የግል ኑሮአቸውንም አሁን የሚገኙበትን የበጎ አድራጎት ሥራ ጎን ለጎን በማስኬድ ደፋ ቀና እያሉ ነው። የበጎ አድራጎቱ ሥራ ዘለቄታ እንዲኖረው ለማድረግ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤተል በሚባለው አካባቢ አምስት ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ለግንባታ ፈቅዶላቸዋል። ወይዘሮ ሐናን በዚህ ቦታ ላይ ስለሚገነባው ህንጻ እንደነገሩን፤ የሚገነባው ህንፃ በማዕከሉ የሚሠጠው አገልግሎት ቋሚ ገቢ እንዲኖረው ለንግድና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ክፍሎች እንዲኖረው ይደረጋል። በጎ ፈቃደኞችና ለጋሾች ከሚያደርጉት እገዛ በተጨማሪ ገቢ ሲኖረው አሁን ላይ የደጋፊዎች እጅ ሲያጥር የሚኖረውን ጫና ይቀንሳል። በመጨረሻም ወይዘሮ ሐናን ለህንጻው ግንባታም የበጎ ፈቃደኞችን እገዛ እንደሚጠብቁ እንዲሁም ሁሉም ሰው ለወገኑ በበጎ እንዲቆም ጠይቀዋል።



# ባህልና ቱሪዝም

# የማንነት መሠረትን የማወቅና የማሳወቅ ሀገራዊ ጥሪ

**ዳግም ከበደ**

በኢትዮጵያ በርካታ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላት የሚከበሩባት ሀገር ነች። ከዓውደ ትዕይንቶች ባሻገር የሀገሪቱ ሕዝቦችን ቀደምት ሥልጣኔ የሚያሳዩ፣ የታሪክ መሠረትን የሚያንፀባርቁ ሀብቶች በስፋት ይገኙበታል። ሀገሪቱ በተፈጥሮ፣ በባህል፣ በሥነ-ፅሁፍና የጥበብ ውጤቶች፣ በቅርስ፣ በአርኪዮሎጂ ታድላለች። የብዝሀ የቱሪዝም መስህብ መገኛ ሀገርም እንደሆነች የሚያሳዩ አያሌ መረጃዎች አሉ። ሶስት ሺህ ዘመናትን የተሻገረ ታሪክና የመስህብ ሀብት ዛሬም ህያው በሆኑ ማስረጃዎች ቁልጭ ብለው ይታያል።

ይህን ሀብት ወደ ቱሪዝም መስህብነት መቀየር እና ከዚያም ተጠቃሚ ከመሆን አኳያ ገና ብዙ መሥራት ይኖርበታል። ሀገሪቱ ይህንን ሀብት ለዓለም ሕዝብ ከማስተዋወቋ አስቀድሞ ዜጎቿ በተለይም አዲሱ ትውልድ ይህን ሀብት በቅጡ እንዲያውቀውና የማንነቱን መሠረት እንዲገነዘበው ማድረግ ላይ መሥራት ይገባል።

‹‹ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ አበዳሪ አይቀበለውም›› እንደሚባለው ሀገርኛ ብሂል የማንነት መሠረት የሆነንን፣ ኢትዮጵያዊ ያሰኘንን የኩራታችን ምንጭ የሆነውን ታሪክ፣ ባህል፣ መልከዓ-ምድር እንዲሁም የመስህብ ሀብት ሁላችንም ጠንቅቀን ማወቅ ይጠበቅብናል። ይህ ሲሆን ነው አንገታችንን ቀና አድርገን፤ በድፍረትና በእውቀት ቀሪው ዓለምን ‹‹ተጋበዙልን ›› ማለት የምንችለው።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት የቱሪዝም ዘርፍ ላይ ትኩረቱን በማድረግ እየሠራ ይገኛል። በተለይ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን እንዲያውቁ እያበረታታ ነው። የባህል የታሪክና የተፈጥሮ መስህቦችን በማስተዋወቅና ዜጎች እነዚህን ሀብቶች እንዲጎበኙ፣ ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖራቸው ግፊት እያደረገ ነው። ለዚህም በቱሪዝም ሚኒስቴር አማካኝነት ‹‹ልወቅሽ ኢትዮጵያ›› የሚል ንቅናቄ ቀርፆ ኢትዮጵያውያንና፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን እንዲያውቁ ቅስቀሳ እየተደረገ ይገኛል።

በተለይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንዲገቡና ከባህልና ታሪካቸው ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ጥሪ በማድረግ ከዚህ ቀደም የነበረውን የተዳከመ የጉብኝትና የግንኙነት መስመር ለመስበር ጥረት እያደረገ ነው።

ከሰሞኑም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በውጭ ሀገሮች የሚኖሩት ‹‹ሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን›› ወደ ሀገራቸው እንዲመጡና ከታሪክ፣ ባህልና ማንነታቸው ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ ጥሪ አቅርበዋል። የቱሪዝም ሚኒስቴርም ይህንን አስመልክቶ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንዲመጡ የተያዘውን መርሀ-ግብር አስመልክቶ ማብራሪያ ሰጥቷል።

በውጭ ሀገሮች ለሚኖረው ለእዚህ ሁለተኛው ትውልድ በተደረገው ጥሪ መሠረት የተቋቋመውን ብሔራዊ ምክር ቤት በሰብሳቢነት የሚመራው የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት፤ ‹‹ወደ ትውልድ ሥፍራችሁ ተመለሱ›› የሚል ስያሜ የተሰጠው የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጥሪ በሶስት ዙሮች የሚካሄድ ነው።

በዚህ መሠረትም የመጀመሪያው መርሀ ግብር ‹‹ከብዝኃ-ባህል መሠረትዎ ጋር ይገናኙ›› በሚል መሪ ሃሳብ ከታህሳስ 20 እስከ ጥር 30 ይካሄዳል። ይህ ወቅት ደግሞ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የገናና የጥምቀት በዓላት የሚከበሩበት መሆኑ ይታወቃል። በዓላቱ በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ዘንድ በልዩ ሁኔታ በድምቀት የሚከበሩ መሆኑ ለመርሃ-ግብሩ ተግባራዊነት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል።

በሁለተኛው ዙር የሚካሄደው የትውልደ ኢትዮጵያውያን መርሀ ግብር ደግሞ ‹‹ታሪካዊ መሰረትዎን ይወቁ›› በሚል መሪ ሃሳብ የሚካሄድ ይሆናል፤ ይህም መርሀ ግብር ከየካቲት 20 እስከ ሚያዝያ 30 ድረስ እንደሚካሄድ ሚኒስትሯ አመልክተው፤ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ተገኝተው የኢትዮጵያን ታሪክ በሚገባ የሚያውቁበት፣ ከማንነታቸው ጋር ትስስር የሚፈጥሩበት ይሆናል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል።

በተጨማሪም በሶስተኛው ዙር ‹‹ዐሻራዎን ያኑሩ፣ የእረፍት ጊዜዎን ያጣጥሙ›› በሚል ከሰኔ 10 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ መስከረም 20 ቀን 2017 ዓ.ም እንደሚካሄድ ሚኒስትሯ አብራርተዋል። በሂደቱም በኢትዮጵያ ውስጥ ሁለተኛው ትውልድ የዲያስፖራው የማህበረሰብ ክፍል የሀገሪቱን የመስህብ ሀብቶች በመጎብኘት፣ በመዝናኛ




**በትውልደ ኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያን መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ዜጎች ከኢትዮጵያ ባህል፣ ታሪክ፣ ወግና ልዩ ልዩ እሴቶች ጋር እንዳይራራቁ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል**

ሥፍራዎችና ሌሎች የእረፍት ቦታዎች ጊዜያቸውን በማሳለፍ ቆይታ እንደሚያደርጉበት አስታውቀዋል።

ሚኒስትሯ በውጭ ሀገሮች ለሚኖሩት ሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ሀገሪቱ ጥሪ የመደረጉ ምክንያት የሀገር ፍቅር ስሜታቸው እንዲዳብር እና ከሀገራቸው ጋር ያላቸው ትስስር እንዲጠናከር ለማስቻል መሆኑን አስታውቀዋል።

ጥሪውን ተቀብለው ወደ ሀገራቸው ለሚመጡ ለእነዚህ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ ትኬት ቅናሽ እንደሚደረግላቸውም ገልፀዋል። ሆቴሎች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች የትራስፖርት አገልግሎት አቅራቢዎች ልዩ የዋጋ ቅናሽ አድርገው ለማስተናገድ መዘጋጀታቸውን ነው የተናገሩት። በተለይ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት መጉላላትና አላስፈላጊ ጉዳዮች እንዳይገጥማቸው የተቀላጠፈ የጉምሩክና ኢሚግሬሽን አገልግሎቶች ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውንም ገልጸዋል።

‹‹በውጭ ሀገሮች የሚገኙት እነዚህ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከሀገራቸው ጋር እንዲቀራረቡ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል›› የሚሉት አምባሳደሯ፤ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጥሪ ቀርቦላቸው ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውንም አስታውሰዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም በተለያዩ ጊዜያት በውጭ ሀገራት ተገኝተው እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች በማግኘት እንዳወያዩና በዚህም የተነሳ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች እና መነሳሳት ተፈጥሮ ትውልደ ኢትዮጵያውያኑ ወደ ሀገራቸው መምጣትና ትስስር መፍጠር ችለዋል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለፃ፤ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው እንዲመጡ ማድረግ ተችሏል። ነገር ግን የትውልድ ቅብብሎሽ አስፈላጊ በመሆኑ ምክንያት ሁለተኛው ትውልድ ዲያስፖራ ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈልጓል። በዚህም እነርሱ ወደ ሀገራቸው እንዲመጡ መጋበዝና ከወላጆቻቸው ሀገር፣ ባህል ታሪክ ጋር ትውውቅና ጥብቅ ትስስር እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈልጓል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ በትውልድ መሃል ቅብብሎሽ እንዳይኖር እና ክፍተት እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል።

ይህ ሀገራዊ ጥሪ ዝርዝር ዓላማዎች ያሉት መሆኑን የተናገሩት ሚኒስትሯ፤ በትውልድ መካከል ድልድይ መገንባት ትልቅ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን ነው ያመለከቱት። በትውልደ ኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያን መካከል ያለውን ክፍተት ለማጥበብ እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ዜጎች ከኢትዮጵያ ባህል፣ ታሪክ፣ ወግና ልዩ ልዩ እሴቶች ጋር እንዳይራራቁ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል።

በዚህ ረገድም በተለያዩ ሀገራትም ተመሳሳይ ልምድ እንዳለም ጠቅሰው፣ በተለይ እንደ እስራኤልና ቻይና የመሳሰሉት ሀገራት መሰል ፕሮግራሞችን በመቅረፅ ትውልዶች ከሀገራቸው ጋር ጥብቅ ትስስር እንዲኖራቸው መሥራታቸው ተጠቃሚ ያደረጋቸው መሆኑን አመልክተዋል።

ከዝርዝር ዓላማዎቹ መካከል አምባሳደሯ በሁለተኝነት ያስቀመጡት ሁለተኛው ትውልድ የዲያስፖራ ማህበረሰብ ክፍሎች ሀገራቸውን ካወቁ በኋላ ለሌላው የዓለም ክፍል እንዲያስተዋውቁና የአምባሳደርነት ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ይህም የቱሪዝም ዘርፉ ለማስፋት ከሚኖረው ፋይዳ ባሻገር ከልዩ ልዩ ዘርፎች የኢንቨስትመንት አማራጮችን ከማስፋት አኳያ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ነው ያስረዱት።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ይህንን ጥሪ እየመራ የሚገኘው ለሀገር ውስጥም ሆነ ለቀሪው ዓለም ማስተዋወቅ የሚችላቸው በርካታ የቱሪዝም ሀብቶች በመኖራቸው እንደሆነ የሚገልፁት አምባሳደሯ፤ ይህንን ኢትዮጵያውያን እራሳቸው እንዲያውቁት እንዲሁም ለሌሎች የዓለም ክፍሎች በአምባሳደርነት እንዲያስተዋውቁ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል። ይህ ጥረት በውጭ ያሉት ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን እነዚህን በርካታ የቱሪዝም ሀብቶች እንዲያውቁ በሀገራቸውም ኩራት ተሰምቷቸው እንዲያስተዋውቁና ለቱሪስት ፍሰቱ መጨመር አስተዋፆ እንዲያደርጉ ያስችላል ሲሉም አብራርተዋል።

‹‹እዚህ ያሉ ኢትዮጵያውያን የሁለተኛው ትውልድ የዲያስፖራ ወጣቶች ለነገ የሀገሪቱ እጣ ፈንታ ወሳኝ መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርባቸዋል›› ያሉት አምባሳደር ናሲሴ፤ ምክንያቱን ሲያብራሩ ሀገር የምትገነባው በውስጥም በውጭም በሚኖሩ ዜጎቿ እንደሆነ ገልፀዋል። በመሆኑም እነዚህ ዜጎች የተለየ ስሜት እንዳይሰማቸውና የኢትዮጵያ አካል እንደሆኑ እንዲያውቁ በሀገር ውስጥ የሚኖሩ የሁሉም ዜጎች ሃላፊነት እንደሆነ አብራርተዋል። በመሆኑም ይህንን ሃላፊነት ኢትዮጵያውያን ተቀብለው ጥሪ የተደረገላቸውን የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያንን ተቀብለው እንዲያስተናግዱም ጥሪ አቅርበዋል።

## እንደ መውጫ

አምባሳደር ናሲሴ ቀደም ሲልም በመግለጫቸው እንዳብራሩት ኢትዮጵያ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ወደ ሀገራቸው እንዲመጡ ይፋዊ ጥሪ ስታደርግ ይህ የመጀመሪያዋ አይደለም። ከዚህ ቀደም የኮቪድ ወረርሽኝና ግጭት በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የፈጠረውን መፋዘዝ ለመቀልበስና ዘርፉን ለማነቃቃት እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ዜጎች ከሀገራቸው ጋር የጠበቀ ትስስር እንዲኖራቸው ለማስቻል በማለም ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ ጥሪ ተደርጎ ነበር።

በዚህም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከበሩ ዓመታዊ ሃይማኖታዊ በዓላት፣ ባህላዊ ፌስቲቫሎች እንዲሁም ልዩ ልዩ ወቅቶችን ተጠቅመው ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲመጡ ተደርጎ ነበር ። በዚህም አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው ገብተው በታቀደው መሠረት አጋርነታቸውን አሳይተዋል። በወቅቱም በርካታ ከዚህ ቀደም ወደማያውቋቸው የሀገሪቱ ክፍሎች ተጉዘው ባህልን፣ ታሪክን፣ ተፈጥሮን መመልከትና ስለሀገራቸው በቂ እውቀት እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። የእረፍት ጊዜያቸውንም በመዝናናትና ከወገኖቻቸው ጋር በመሆን አሳልፈዋል። ወደ መጡበት ሲመለሱም ለቀሪው ዓለም ኢትዮጵያን በአምባሳደርነት ወክለው አስተዋውቀዋል ።

በዚህ ሥራ ለብዙዎች የሥራ እድል ከመፍጠር ባሻገር የተቀዛቀዘው ቱሪዝም ዳግም እንዲያንሰራራ ትልቅ ሥራ መሠራቱንም ነበራቸው። ለዚህም ነው የትውልድ ቅብብሎሹ እንዲቀጥልና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሩቅነት ስሜት እንዳይሰማቸው በቀጣይነት ይህንን ጥሪ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ኢትዮጵያ የሺህ ዘመናት የሀገረ-መንግሥት ታሪክ፣ ውብ ባህልና ማንነት ያላቸው ብሔረሰቦች በጋራ ተዋደውና በአንድነት ተጋምደው የሚኖሩባት ሀገር መሆኗ በገሃድ የሚታይ ሃቅ ነው። ይህንን በውጭ ተወልደው ያደጉ (የሁለተኛው ትውልድ) ኢትዮጵያውያን ማወቅ ይገባቸዋል። ሕዝቦቿ ለአይን ማራኪ፣ ጆሮ ገብና ተወዳጅ የሆኑ እሴቶች ባለቤት ፤ ባህልና ወጋቸው ለባዳው የሚያስቀና ለወዳጅ ሃሴትን የሚፈጥር መሆኑን በአካል መጥተው ማወቅና የዚያ እሴት ተጋሪ የመሆን መብትም አላቸው።

ኢትዮጵያውያን ጠላትን በአንድነት መክተው ድባቅ የሚመቱ ለሉዓላዊነታቸው መከበር በጋራ ዘብ የሚቆሙም መሆናቸውን እዚሁ ሀገራቸው ድረስ መጥተው ከዓድዋ ድል ታሪክና ከሌሎችም ታሪካዊ ሀብቶች መገንዘብ አለባቸው የሚል እምነት አለን። ሁሉም ዜጎች ኢትዮጵያዊነትን ሳይለቁና የመጡበትን ማህበረሰብ ባህልና ማንነት ሳይሸራርፉ አብረው የመኖር የሺህ ዓመታት ታሪክ ባለቤትም መሆናቸውንም ከፈረሱ አፍ መስማት ይገባቸዋል። እነርሱም የዚህ ታሪክ፣ ባህል ውብ ሀገር ባለቤት እንደሆኑ ለማወቅ ይህ ሀገራዊ ጥሪ በእጅጉ አስፈላጊ መሆኑን የዝግጅት ክፍላችንም እምነት ነው።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ‹‹ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?››

ዋለልኝ አየለ

ይህ ድምጽ በተለምዶ ‹‹የ60ዎቹ ትውልድ›› እየተባለ የሚጠራው የዚያ ትውልድ ተማሪዎች ድምጽ ነበር። ‹‹ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ!›› የጥላሁን ግዛውን አገዳደል ፍትሕ የሚጠይቅ የተማሪዎች መፈክር ነበር። ጥላሁን ግዛው የተገደለው ከ54 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ነበር። ለመሆኑ ጥላሁን ግዛው ማነው? ለምን ተገደለ? በማን ተገደለ? የሚሉ ጥያቄዎችን የታሪክ ሰነዶችን ዋቢ አድርገን በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን እናስታውሰዋለን። ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ የዚህ ሳምንት የታሪክ አጋጣሚዎችን እናስታውስ።

ከ36 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 17 ቀን 1980 ዓ.ም ኢትዮጵያ የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ የእግር ኳስ ሻምፒዮና ዋንጫ (ሴካፋ) ለመጀመሪያ ጊዜ አሸነፈች። ኢትዮጵያ ባስተናገደችውና ስምንት ሀገራት (ኢትዮጵያ፣ ዚምባብዌ፣ ዛንዚባር፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ኡጋንዳ፣ ዛምቢያ እና ማላዊ) በተካፈሉበት 15ኛው የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ የእግር ኳስ ሻምፒዮና ዋንጫ (ሴካፋ) ለፍፃሜ የቀረቡት አስተናጋጇ ኢትዮጵያ እና ዚምባብዌ ነበሩ። የወቅቱ የሁለቱ ሀገራት መሪዎች ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም እና ሮበርት ሙጋቤ ነበሩ። ይህ ጨዋታ በዝነኛው የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ‹‹...ወይኔ! ወይኔ ዳኙ! ዳኙ አገባ!...›› በሚለው አይረሴ ድምጽ ይታወሳል። የዚህን ታሪክ ዝርዝር ባለፈው ዓመት ታኅሳስ 23 ቀን 2015 ዓ.ም የታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሳምንቱ በታሪክ ዓምድ ላይ ማግኘት ይቻላል።

ከ32 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ዴሴምበር 26 ቀን 1991 (በኢትዮጵያ ታኅሳስ 17 ቀን 1984 ዓ.ም) የሶቪየት ሕብረት መበታተን በይፋ ታወጀ። እነሆ አሁን ሩሲያ (ራሽያ) በሚለው ስሟ ትጠራለች። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ ከነበሩት ሀገራት አንዷ በመሆን ከአራቱ የዓለም ልዕለ ኃያላን ሀገራት (አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ሶቪየት ሕብረት) አንዷ የነበረችው ሶቪየት ሕብረት በኋላ ከአሜሪካ ጋር ‹‹ቀዝቃዛው ጦርነት›› የሚባለው ጦርነት ውስጥ ገባች። አሜሪካ የምዕራቡን ዓለም፣ ሶቪየት ሕብረት የምሥራቁን ዓለም አጋር እያደረጉ ጎራ ፈጠሩ። እንዲህ እንዲህ እያለ የቀጠለው የሶቪየት ሕብረት ጉዳይ በ1984 ዓ.ም በይፋ ፈረሰ። እነሆ የሶቪየት ሕብረት መፍረስ በብዙ ፖለቲከኞችና የታሪክ ባለሙያዎች በየአጋጣሚው ሲጠቀስ እንሰማለን።

ከ116 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሳስ 20 ቀን 1900 ዓ.ም በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያዋ መኪና ወደ አዲስ አበባ ገባች። እነሆ የመጀመሪያዋ መኪና እየተባለችም በታሪክ ትጠቀሳለች።

በዕለቱ በዝርዝር የምናየው ታሪክ በንጉሣዊ ሥርዓቱ ጊዜ የግራ ዘመም አራማጅ የነበረውን የጥላሁን ግዛው መገደል እና የነበረውን የተማሪዎች እንቅስቃሴ እናስታውሳለን።

ጥላሁን ግዛው የተገደለው ከ 54 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ነበር። የጥላሁን መገደል ሲሰማ ‹‹ጥላሁን ለምን ተገደለ?›› በሚል በተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ተቀስቅሶ ነበር። በነገራችን ላይ ‹‹ኀብር ሕይወቴ›› በሚል ከወራት በፊት የታተመው የፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ የግል የሕይወት ታሪካቸው መጽሐፍ ያንን ክስተት ያስታውሳል። የታኅሳስ ግርግርን በዓይናቸው አይተው እንደነበረው ሁሉ በጥላሁን ግዛው መገደል የተፈጠረውን የአባታቸውን ጭንቀት እና የነበረውን ሁነት አስታውሰዋል።

ወደ ታሪኩ ስንመለስ፤ በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የግራ ዘመም ፖለቲከኞች ስብስብ ተጠናክሮ አዞዎች (ክሮኮዳይልስ) የተሰኘ ቡድንን በመፍጠር 1957 ዓ.ም የኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል መርህ ‹‹መሬት ላራሹ›› መሆኑ ይፋ ተደረገ። መጋቢት 4 ቀን 1957 ዓ.ም ‹‹መሬት ላራሹን የምትሹ፤ ተዋጉለት አትሸሹ›› እያሉ ተማሪዎች በአደባባይ ሰልፍ በወጡበት ወቅት የ11ኛ ክፍል ተማሪ የነበረው ጥላሁን በሰልፉ ተሳትፏል።




ጥላሁን ግዛው የ«አዞዎቹ» ዓላማ አራማጅና በኋላም ለመሪነት ለመታጨት የበቃ ወጣት ነበር። በ1961 ዓ.ም በተደረገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በመኮንን ቢሻው ቢሸነፍም በቀጣዩ ዓመት ኅዳር 1962 ዓ.ም በተደረገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በከፍተኛ ድምጽ ብልጫ አሸንፏል። ጥላሁን የፕሬዚዳንትነት ዘመኑ ቀዳሚ ሥራው የተማሪውን የመናገር፣ የመጻፍና የመደራጀት ነጻነት ይበልጥ ማጠናከር ነበር። ለሁለት ወር ብቻ በፕሬዚዳንትነት የቆየው ጥላሁን የተለያዩ ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩ በማበረታታት የሚታወቅ ታጋይ ነበር ይባልለታል።

ታኅሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ምሽት አንድ ሰዓት አካባቢ ከታናሽ ወንድሙ መኮንን ሲሳይ ጋር በመሆን ከስድስት ኪሎ በስተጀርባ አፍንጮ በር በሚባለው አካባቢ ፍቅረኛውን ዮዲት ታዬን ለመሸኘት ወጥተው ታርጋ በሌለው መኪና በተተኮሰ ጥይት ተገደለ።

ሱልጣን አባዋሪ የተባሉ ሰው ‹‹የተማሪው ትግልና የአብዮቱ ደመና›› በሚል ርዕስ አንታዛ መጽሄት ላይ ባቀረቡት ጽሑፍ የጠቀሷቸው ሌተናል ኮሎኔል ፍስሐ ደስታ ስለአሟሟቱ ሲገልጹ፤ ‹‹ስለ ጥላሁን ግድያ የተለያዩ ነገሮች ቢወሩም ... ሐቁ ግን ግድያው የተፈፀመው በንጉሡ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ፣ የንጉሡ የቅርብ አጃቢ ወይም አንጋች ክፍል ምክትል አዛዥ በነበሩት በኮሎኔል ጣሰው ሞጃ ትዕዛዝና ከብሔራዊ ጦር ተዛውረው እኔው ራሴ ደብረ ብርሃን ካሰለጠንኳቸው በኋላ የአንጋች ክፍል ባልደረባ በሆኑት ሁለት ወታደሮች ነበር። ለዚሁ ድርጊታቸውም ሁለቱም የምክትል መቶ እልቅና ማዕረግ የተሰጣቸው መሆኑን የድርጊቱ ፈፃሚዎች ነግረውኛል›› ብለዋል።

በግድያው የተቆጡ ተማሪዎች የጥላሁንን አስከሬን ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ስድስት ኪሎ) ቅጥር ጊቢ በመውሰድ ከአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመጡ ተማሪዎች ጋር የኀዘኑ ተካፋይ ሆኑ። የጥላሁን ታሪክና የትግል ዓላማ በግጥምና በስድ ንባብ እየተሰማ የኀዘን መግለጫው ዝግጅት ተካሄደ።

**በግድያው የተቆጡ ተማሪዎች የጥላሁንን አስከሬን ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ስድስት ኪሎ) ቅጥር ጊቢ በመውሰድ ከአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመጡ ተማሪዎች ጋር የኀዘኑ ተካፋይ ሆኑ**

ቀጥሎም በተማሪዎች ሰልፍ ታጅቦ በክብርና በጀግንነት በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ይፈጸም ዘንድ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ያደረጉት ጥረት በንጉሡ ጸጥታ ኃይሎች ርምጃ የተጨማሪ ተማሪዎችን ሕይወት ቀጥፎ አስከሬኑ ከተማሪዎቹ ተወሰደ።

የጥላሁን ግዛው አስከሬን ከተማሪዎቹ በኃይል ርምጃ ከተወሰደ በኋላ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ታህሳስ 22 ቀን 1962 ዓ.ም መላው ዘመድ አዝማድ በተገኙበት በአካባቢው ተማሪዎች ሰልፍ አጃቢነት በወቅቱ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት በማይጨው ሕዝባ ማርያም ቤተክርስቲያን ተፈጸመ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄም የጥላሁንን መገደል አስመልክቶ ባለ ሰባት ነጥብ የአቋም መግለጫ አወጥቶ ነበር። የመግለጫው ጥቅል መልዕክት፤ በጥላሁን መገደልና መገደሉን ተከትሎም በተከሰተው ተጨማሪ ጥፋት ሁሉ የወቅቱን ገዥ መንግሥት (የንጉሡን ሥርዓት) ተጠያቂ የሚያደርግ ነበር።

የተማሪዎች እንቅስቃሴም የበለጠ ተቀጣጠለ። ‹‹የጥላሁን ገዳዮች እኛንም ግደሉን! ጨርሱን! ተኩስ! እስቲ በል ተኩስ! ፋሽስት!›› የሚሉ መፈክሮችና ቁጣዎች ተጠናክረው ተቀጣጠሉ። ይህ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ቀጥሎ ከሦስት ዓመት በኋላ ደግሞ ኅዳር 29 ቀን 1965 ዓ.ም የጥላሁን ግዛው የትግል አጋር የነበረው ዋለልኝ መኮንንና ፍቅረኛው ማርታ ተገደሉ። አሁንም ተቃውሞውና መፈክሩ ቀጠሉ።

ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?  
ዋለልኝ ለምን ለምን ሞተ?  
ማርታ ለምን ለምን ሞተች?  
በሃይል በትግል ነው  
ነፃነት የሚገኘው!

እያለ ያ ትውልድ ለቀጣይ ትግል ቅስቀሳ ጀመረ። ዝማሬዎች የየሰልፉ ማድመቂያና መቀስቀሻ ሆኑ። ማንነቱን ለሕዝብ መብትና ነፃነት አሳልፎ ሊሰጥ የተዘጋጀ ትውልድ መሆኑን ደጋግሞ ተናገረ። ወደ ጥላሁን ግዛው እንመለስ።

ጥላሁን ግዛው በአሁኑ አወቃቀር ከደቡብ ትግራዩ የራያና አዘቦ አውራጃ ተወላጅ አባቱና እንዲሁም ደግሞ ከሰሜን ወሎዋ የራያ ቆቦ አውራጃ ተወላጇ እናቱ አብራክ የተወለደ የሁለት ራያ ልጅ መሆኑን ዋልታ ላይ የተሰነደ ታሪክ ያሳያል። ጥላሁን የተወለደውና እንዲሁም ሲሞት የተቀበረው አባትየው አቶ ግዛው አበራ ተድላ ይኖሩበት በነበረው የራያና ዓዘቦ አውራጃ ዋና ከተማ ማይጨው ውስጥ እንደሆነ ወንድሙ ጭምር አረጋግጠዋል። በማይጨው ከተማ የማይጨው ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጥላሁን ግዛው ስም መሰየሙንም የታሪክ ሰነዶች ያሳያሉ።

የጥላሁን ወላጆች ትዳር ሳይሰምር ቀርቶ በፍቺ ለመለያየት እንደተገደዱና እርሱም ገና ከልጅነት ዘመን ዕድሜው ጀምሮ ከእናቱ ጋር ወደ ራያ ቆቦ የሄደበት ሁኔታ ስለመፈጠሩም ታናሽ ወንድሙ ተናግረው እንደነበር የዋልታ ዘገባ ያሳያል።

ስለጥላሁን የተጻፉ ሰነዶች እንደሚያሳዩት፤ ጥላሁን ግዛው ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፋዊ የስርነቀል ለውጥ ፍለጋ ንቅናቄ መሪ ተዋንያን የተለየ የሚያደርገው መሠረታዊ ምክንያት፤ በአባቱ ወገን ከትግራይ ታላላቅ መሳፍንቶች መካከል አንዱ ከነበሩትና በተለይም የራያ ዓዘቦ አውራጃ ዋና ከተማ የሆነችውን ማይጨውን እንደቆረቆሯት ከሚነገርላቸው ከደጅ አዝማች ተድላ ገብረ ዋህድ ቤተሰብ የተገኘ ሆኖ ሳለ፤ የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴን ዘውዳዊ አገዛዝ ታግሎ ስለማስወገድ አስፈላጊነት በመገንዘብ የስርነቀል ለውጥ አቀንቃኝ መሆኑ ነው።

የአሁኑ ትውልድ ምናልባትም ከዚህ ሊማረው የሚገባው ነገር፤ የጋብቻ መተሳሰር፣ የብሄርና የሃማኖት ወገንተኝነት፣ የራሴ ወገን ነው... የሚሉ ነገሮች የጋራ ዓላማ እንዳይኖር የሚያደርጉ መሆኑን ነው። ለድጋፍም ይሁን ለተቃውሞ የጋራ ዓላማ እንጂ የግል እና የቡድን ፍላጎት የጋራ ሀገር አይገነባም።

ሌላው ልብ መባል ያለበት ነገር፤ በተለምዶ ‹‹የ60ዎቹ ትውልድ›› የሚባሉ የለውጥ አቀንቃኞች ትግላቸው ምን ነበር? እነማን ምን አደረጉ የሚሉትን በወቅቱ ከነበሩ ሰዎች፣ ወይም በወቅቱ የነበረውን ሁነት ጽፈው ያስቀመጡ ሰዎችን ሰነዶች ማየት ያስፈልጋል። ያ ባለመሆኑ ይመስላል በተለይም የእነ ጥላሁን ግዛው እና ዋለልኝ መኮንን ጉዳይ በተለያዩ አወዛጋቢ (ወጥ ባልሆነ) መንገድ ሲከራከሩባቸው ይሰማል። በመሆኑም በዘመኑ የነበሩ ሰዎች የነበረውን ሁነት ሊጽፉልን ይገባል!

# የዝነኞች ገጽ

## የቀንዲል መስራቹ ጋሽ አያልነህ



**ቤዛ እሸቴ**

ለወጣቱ አያልነህ ሙላት በሩሲያ ኑሮ ተመችቶታል። አካሄዱ በድርሰት ማህበር አማካኝነት ባገኘው የትምህርት እድል ነበር። በሞስኮ ሬዲዮ ጣቢያ የአማርኛ ክፍለ ጊዜ “የገጣሚው ደብተር” የተባለ ዝግጅት ያቀርባል። በትምህርቱም ሁለተኛ ዲግሪውን ከማጠናቀቁም ባሻገር ሦስተኛ ዲግሪውን ሊቀበል ከጫፍ ደርሷል፡፡

በኢትዮጵያ አብዮት ፈንድቷል፤ የለውጥ ጭላንጭል ብቅ ብሏል። በወቅቱ የባህል ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ የነበረው ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን ለጉዳይ ወደ ሞስኮ ባቀናበት አጋጣሚ “ብቻዬን ነኝ፤ ሰው የለኝምና አግዘኝ” ሲል ወጣት አያልነህን ደጅ ጠና። ያኔ አያልነህ የፒኤችዲ ትምህርቱን ወደማጠናቀቅ ተቃርቦ ነበር። ተማሪው አያልነህ ያኔ ትምህርቱን ትቶ ጓዜን፣ ማቄን ሳይል ጸጋዬን ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ። “እሳት ሲነድ” የተሰኘ በሀገረ ሩሲያ የተጻፈ ተውኔቱን ጸጋዬ ይዞት መጥቶ እውቁ አዘጋጅ አባተ መኩሪያ ሲያዘጋጀው፤ ሠአሊና ገጣሚ ገብረክርስቶስ ደስታ መድረኩን አዘጋጅቶ የተዋጣለት ተውኔት በመሆን የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ትያትር ቤት መክፈቻ ሆነ።

### ሀገርን ማገልገል

በባህል ሚኒስቴር ውስጥ የቲያትር ጥበባት ድርጅትን በማቋቋም ትያትር ቤቶችን በሥሩ በማድረግ ሥራውን “ሀ” ብሎ ጀመረ። ይህ የሥራ ጅማሮ የወራትን እድሜ እንዳስቆጠረ፤ ጊዜው የአብዮት ነውና ከሩሲያ እናት ሀገሩን ሊያገለግል የተመለሰው አያልነህም ሆነ እንዲመለስ ጠሪው ሎሬት ጸጋዬ ማረፊያቸው እስር ቤት ሆነ። ጋሽ አያልነህ የታሰረው ጽፎ ለሳንሱር ክፍል በቀረበው “ሻጥር በየፈርጁ” በተሰኘው ቲያትር ላይ “በደርግ መቃብር ላይ ሕዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ትገነባለች፡፡” የሚል አረፍተ ነገር በማግኘታቸው መሆኑን ይናገራል።

ትያትሩ ገና የግምገማ ሂደቱን ያልጨረሰና ሴንሰር ይፍቀደው፣ አይፍቀደው አልታወቀም ነበር። በመሆኑም ቢፈልጉ ኖሮ ቁረጠው ወይም በሌላ ተካው ማለት ይችሉ የነበረ ቢሆንም ምክንያት ይፈልጉ ስለነበር ነው ይላል። ከአንድ ቀን የእስር ቤት ቆይታ በኋላ ቢፈታም፤ ወደ ቀድሞ ሥራው መመለስ የማይታሰብ ሆነ። ይልቁንስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲያስተምር ይሁንታን አገኘ። በዩኒቨርሲቲው የሥነ-ጽሁፍ መምህር በመሆንም ሕይወት ቀጠለ።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሳለ ትያትር ይሠራበት የነበረው በቀድሞ ኪነ-ጥበባት ወቲያትር ይባል የነበረው ተዘግቶ የቤተመጻሕፍት መጽሐፍ መደርደሪያ ሆኖ አየው። በዚህ ቅር የተሰኘው አያልነህ የዩኒቨርሲቲውን ፕሬዚዳንት “እባክህ ፍቀድልኝና ልክፈተው” ሲል ተማጸነ። ፕሬዚዳንቱ ከማስተካከያ የተወሰነ ብር ጋር ፍቃዳቸውን ቸሩ። ያኔ መደርደሪያው ወጥቶ፣ አዳራሹ ታድሶ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማእከል ተቋቋመ። በዚህ የተነሳም በኢትዮጵያ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የባህል ማእከል ያቋቋመ የመጀመሪያው ሰው ለመሆን በቃ።

የባህል ማእከሉን ያቋቋመው ማእከሉን ከሚመሩ የቦርድ አባላት ጋር ነው። የሥነ-ጽሁፍ ዘርፉን የሚመራው ዶክተር ኃይሉ አርአያ የተባሉ የሥነ- ጽሁፍ ባለሙያ፣ የቲያትሩን ዘርፍ የሚመራው ደበበ ሰይፉ፣ የጋዜጠኝነትና የውይይት ዘርፉ የሚመራው በእውቁ ጋዜጠኛ ነጋሽ ገብረማርያም፤ የዘመናዊ ሙዚቃው የሚመራው በኢትዮ-ጃዝ ፈጣሪው ሙላቱ አስታጥቄ፤ የባህላዊ ሙዚቃው በተስፋዬ ለማ እንዲመራ በማድረግና እነዚህን ጎምቱ ሰዎች የባህል ማእከሉ የቦርድ አባላት በማድረግ፤ ጋሽ አያልነህ ሙላት የቦርድ ሰብሳቢ በመሆን የባህል ማእከሉ ወደ እንቅስቃሴ ገባ። በየቀኑ አምስቱም ዘርፎች ፕሮግራም ነበራቸው። በዚህ ሂደት የዩኒቨርሲቲው የባህል ማእከል እስካሁን የሚታወስበትን “እንኳን ደስ አላችሁ”፣ “አባይ አባይ” እና መሰል ሕብረ ዝማሬዎችን አበርክቷል።

በባህል ማእከሉ ትልቅ ሥራ ቢሠራም በሚያስተምርበት የትምህርት ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ዩኒቨርሲቲውን ለቆ አስመራ ዩኒቨርሲቲ የፐብሊክ ሪሌሽን ኃላፊ ሆኖ እንዲሄድ ተስማምተናል ብለው በመፈራረም በወቅቱ ለነበረው ከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን (ሀየር ኮሚሽን) አቀረቡ። የቀረበለት አካልም በዝውውር ሃሳቡ በመስማማት በአስቸኳይ ወደ አስመራ እንድትሄድ የሚል ደብዳቤ እንዲደርሰው ያደርጋል። “አልሄድም!” የሚል ሙግት ገጥሞ ባለበት ሰዓት እምቢ የማይባል ሌላ ፈላጊ ይገጥመዋል። እሱም “ኢሰፓኮ” በኋላ “ኢሰፓ” የተሰኘው የደርግ ፓርቲ መቋቋሙን ተከትሎ፤ በሦስት ቀን ውስጥ በእጁ የሚገኙ ንብረቶችን አስረክቦ ማእከላዊ ኮሚቴ እንዲመጣ የሚል ደብዳቤ ደረሰው። “አማራጭ አልነበረኝምና ሁሉን ነገር ትቼ ኢሰፓ ውስጥ ገባሁ፡፡” ይላል።

17 ዓመታት ከደርግ ጋር ሠርቷል፤ በዚህ ሒደትም “ሕዝብ ለሕዝብ” ላይ አስተባባሪ ሆኖ የመሳተፍ እድል አግኝቷል። ጋሽ አያልነህ ሕዝብ ለሕዝብ ቡድኑ የተደራጀው ለሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ መልስ የሚሰጥ ቡድን እንዲሆን ተደርጎ መሆኑን ያነሳል። በዚህም እነማይክል ጃክሰን እራሱ እስክስታን እየጨፈሩ ከየት አመጣኸው ሲባል “ከፒውፐል ቱ ፒውፐል” ማለት መጀመራቸውና ይህም ትልቅ ስኬት መሆኑን ይናገራል። ሕዝብ ለሕዝብ ምእራባውያን ለረዥም ጊዜ ባህል እያመጡ ሲጭኑ የነበረውን የማስቀረትና የኢትዮጵያን ባህል ለሌሎች ሀገራት የሚያሳይ ቡድን ለመፍጠር መሥራቱን ይናገራል። ያም ቢሆን እስካሁን በስኬት ስሙ የሚነሳው ቡድን ሲመለስ ቡድኑ ከመፍረሱም ባሻገር የቡድኑ የኪነ-ጥበብ ዘርፍ መሪ የሆነው ጋሽ አያልነህ 17 ክሶች ጠብቀውታል፡፡

በወቅቱ ጋሽ አያልነህ ወደ ሀገርህ ብትገባ እስር ቤት ነው የምትገባው ስለተባለ ከቡድኑ ጋር ወደ ሀገር ቤት አልገባም። በዛው ጥፋ የሚል ምክር ቢለገስም ቡድኑ ሐሙስ ገብቶ እሱ ቅዳሜ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ሀገር ውስጥ እንደገባ እንደተፈራው እስር ቤት ባይገባም ከሥራው ታግዶ የቀረበበትን 17 ክስ የሚያጣራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ትልልቅ ባለሥልጣናት ጉዳዩን ማጣራት ጀመሩ። ያኔ ታዲያ ደሞዙን ባይከለከልም ከሥራው ታግዶ ሲፈለግ ቀርቦ ለጥያቄያቸው መልስ እየሰጠ ባለበት ደርግ ወድቆ ኢህአዴግ ሥልጣን ተቆጣጠረ። ያኔ ክሱን መጣራቱ ቀርቶ ወደ ዩኒቨርሲቲ ተመለስ የሚል ደብዳቤ ደረሰው። ወደ ዩኒቨርሲቲ ተመልሶ ለስምንት ወራት እንደቆየ ከ40 መምህራን ጋር ጊቢውን ለቀህ እንድትወጣ የሚል ሌላ ደብዳቤ ደረሰው። የባህል ማእከሉ ዘማሪ የነበሩ 17 ዘማሪያንም አብረው እንዲወጡ ተደረገ።

### ብሶት የወለደው ቀንዲል

ከባህል ማእከሉ የተባረሩት 17 ዘማሪያን ወደ ጋሽ አያልነህ በመምጣት “አንተ ብቻ ሳይሆን እኛም አብረንህ ወጥተናልና መላ ፍጠር” አሉት። ያኔ ታዲያ የኪነ-ጥበብ ጥሙንም ለማርካት እና ለእሱም ሆነ ለዘማሪያኑ ገቢ ለመፍጠር በማሰብ ቀንዲል ቤተ-ተውኔት ተፈጠረ። ትያትርን ጨምሮ የተለያዩ የኪነ-ጥበብ ውጤቶችን በጣልያን ባህል ማእከል ማሳየት ጀመሩ። ሁለት የጣልያን ትያትሮችን ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ በመተርጎምና ሁለት የጋሽ አያልነህ አዲስ ድርሰቶችን ትያትር በማሳየት ገቢ ማግኘት ተጀመረ።

ጋሽ አያልነህ ሁኔታውን መለስ ብሎ ሲያስታውስ “ዳቦ እየበሉ ከመኖር ወደ ምግብ ቤቶች ጎራ ማለት ጀመርን” ይላል። ያኔ ታዲያ የባህል ማእከሉም አይቶት የማያውቀውን ሕዝብ ማስተናገድ ጀመረ። ሆኖም በጣልያን አምባሳደር “ለምን ብለህ እንዳትጠይቀኝ ግን ቤቱን ለቀህ ውጣ!” መባሉን ተከትሎ ከጣልያን የባህል ማእከል ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ። ያኔ ታዲያ አማራጭ የለምና በአዲስ አበባ፣ ግንፍሌ አካባቢ የእድር ቤት አዳራሽ ለመከራየት ተገደዱ። የቤቱ አካባቢ ቆሻሻ ከመሆኑ የተነሳ ወደ ትያትር ቤቱ የሚመጣ እንግዳ አፍንጫውን ይዞ ሽታውን ለማምለጥ በጥድፊያ መራመዱ የግድ ነበር።

ቤቱ ዝናብ ሲጥል ጣርያው ያፈስ ነበርና ሥራ የሌላቸው የቡድኑ አባላት ለእንግዶች ጥላ ይይዙ ነበር። ያም ቢሆን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ፣ እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌና ሌሎችም የተከበሩ እንግዶች የቤቱ ደምበኞች ነበሩ። ያም ቢሆን የቡድኑ አባላት ወደ ጊቢው ሊገቡ ሲሉ የፓርቲ አባል የነበሩ ሰው ከ200 በላይ የሚሆኑ የእድሩ አባላትን በመሰብሰብ ቤታችሁን ሊወርሱ ነው በማለታቸው ከእድር ቤቱም ተባረሩ፡፡

ያኔ ታዲያ ጋሽ አያልነህ የሩሲያ የባህል ማእከል በመሄድ በተደጋጋሚ ከመንግሥት ጋር የሚያጋጨው ትያትር ነበርና፤ ትያትር እንደማያሳይ ቃል በመግባትና የባህል ማእከሉ ምክትል ዳይሬክተር በመሆን ለማገልገል በመስማማት ሥራ ጀመረ። በፑሽኪን የቀንዲል ቤተ-ተውኔት እንቅስቃሴ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን፤ በርካታ በጥበቡ ዓለም የሚገኙ ሰዎች ሥራቸውን ለታዳሚ ለማቅረብ እድል የከፈተ መድረክ መሆኑን ይመሰክራሉ። መድረኩ በሀገራችን አሁን ለተስፋፋው የሥነ-ጽሁፍ ምሽት መነሻ መሆኑን በርካታ የሥነ-ጽሁፍ ምሽት አዘጋጆች ይመሰክራሉ። የቀንዲል መድረክ በርካታ ገጣሚያንና የጥበብ ሰዎችን ማፍራት አስችሏል። ቀንዲል በእውቀቱ ስዩም፣ ኤፍሬም ስዩም፣ አበባው መላኩ፣ ምስራቅ ተረፈን ጨምሮ በመላው ኢትዮጵያ በኪነ-ጥበብ ከፍተኛ ቦታ ለደረሱ ሰዎች ልምድ ማግኘት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው።

ቀንዲል ከጋሽ አያልነህ ጋር አብረው የነበሩ የያኔ ታዳጊዎችና ወጣቶች የአሁን አንጋፋዎች፤ ጋሽ አያልነህ ያኔ እምቅ አቅማቸውን ከእነሱ ቀድሞ እያየ አምኖ መድረክ ስለሰጣቸውና ትልቅ ኃላፊነት በመስጠት ያለ ጣልቃ ገብነት፣ በነጻነት ሥራዎች እንዲሠሩ በማድረጉ ያመሰግኑታል። ለጋሽ አያልነህ ማንበብ አያደክምም፤ ለመጻፍም ሃሳብ አያልቅበትም። በዛው ልክ በርካታ ተውኔቶችን ለተመልካች እንካችሁ ይላል። ግን መድረክ ከመነፈግ አንስቶ ከአንድ መድረክ ያልዘለሉ በርካታ ሥራዎች አሉት።

ለጥቁር አፍሪካ ፌስቲቫል በናይጄሪያ የቀረበው “ትግላችን” የተጻፈው በጋሽ አያልነህ ነው። ሙዚቃዊ ተውኔቱ በፌስቲቫሉ ላይ ሦስቴ የመታየት እድል አግኝቷል። ከዛም ባሻገር በናይጄሪያ ዩኒቨርሲቲዎች እየዞረ እንዲታይ የናይጄሪያ መንግሥት በመጠየቁ በዩኒቨርሲቲዎች ለእይታ በቅቷል። ከዛ መልስም በኩባ በነበረው የወጣቶች ፌስቲቫል ላይ እንዲቀርብ ጥያቄ በመምጣቱ ትግላችን በኩባ መድረክም ተመድርኳል። በሁለት አህጉራት የታየው ይህ ትያትር በኢትዮጵያ ግን በአንድም መድረክ አልታየም፡፡

በተመሳሳይ በርካታ የዓለም ሀገሮች የታየው “ሕዝብ ለህዝብ” እራሱ በኢትዮጵያ መድረክ አልታየም። በብሔራዊ ትያትር አንድ መድረክ የተተወነው “የመንታ እናት” ትያትር በወቅቱ የሀገሪቱ መሪ መንግሥቱ ኃይለማርያም የተመረቀና የታየ ከመሆኑ ባሻገር የሀገር መሪውንም ያስለቀሰ ትያትር ነበር። ትያትሩን የታደመ አንድ የደርግ አባል የሶማሌ ገጸ-ባህሪ ወክሎ የሚጫወተውን ተዋናይ በሽጉጥ ካልገደልኩ ብሎ በገላጋይ ቢታገስም፣ ድጋሚ የመሠራት እድል አላገኘም። በተመሳሳይ “መስከረም” የተሰኘውን የባህላዊ ሙዚቃ ድራማ የወቅቱ ምክትል መሪ የነበሩት ፍቅረሥላሴ ወግደረስ መርቀው ቢመለከቱትም ለሕዝብ ይፋ እንዳይሆን ተደርጓል።

የኢህአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘና አያልነህ ሙላትም ከዩኒቨርሲቲ ከተባረረ በኋላ አልጀርስ በሚካሄድ የፓን አፍሪካ ስብሰባ ላይ የሚቀርብ ተውኔት እንዲያዘጋጅ በደብዳቤ መጠየቁን አስመልክቶ “ሉሲ”ን አዘጋጀ። “ሉሲ” የተሰኘው ሙዚቃዊ ተውኔት በአልጀርስ የተሳካ ቆይታ አድርጎ ቢመለስም የሀገር ውስጥ መድረክ ከመከልከል አላመለጠም። እነዚህ የተከለከሉ ተውኔቶች አሁን ድረስ ለምንና ማን ከለከላቸው የሚለው ጥያቄ ሳይመለስ እስካሁን እንቆቅልሽ እንደሆነ አለ።

ባለቅኔ፣ ገጣሚ፣ ጸሀፌ ተውኔት፣ ደራሲ፣ ሰዎች እያፈራረቁም ሆነ በጋራ ከስሙ በፊት የሚጠቀሟቸው ማእረጎች ናቸው። እሱ ግን ከሁሉም በላይ “ጋሽ አያልነህ” ደስ ይለኛል ይላል። በትምህርት፣ ብሎም በሥራ የቆየበትን የሩሲያ ቋንቋ ተክኖታልና በርካታ የሩሲያ ሥራዎችን ወደ አማርኛ ተርጉሟል። በተመሳሳይ የእንግሊዝኛ ተውኔቶችን ወደ አማርኛ መልሷል። የእሱም ሥራዎች ተተርጉመው ለዓለም አቀፍ ማሕበረሰብ የመድረስ እድል አግኝተዋል። “ደሃ አደግ” የተሠኘ ድርሰቱ ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሞ ለሁለት ዓመት በእንግሊዝ ተዋናዮች ለንደን ላይ ተተውኗል። “የመንታ እናት” በሩሲያኛ ተተርጉሞ ለእይታ በቅቷል።

### ፋውንዴሽን

አያልነህ ሙላት ፋውንዴሽን ተቋቁሞ ወደ ሥራ ለመግባት መንገዶችን እየጠረገ ነው። ጋሽ አያልነህ ፋውንዴሽኑ “አለ ለማለት ሳይሆን ሀገር በቀል እውቀት ላይ የተመሠረተ ጥበብን ለመገንባት ያሰበ ነው፡፡” ይላል። ፋውንዴሽኑ በሀገር በቀል እውቀት ላይ የተመሠረተ ትያትር፣ ሙዚቃና ሥነ-ሥዕል ለመፍጠር ያሰበ ነው። እንደ ጋሽ አያልነህ ማብራሪያ አዲሱን ትውልድ አስኳላ አበላሽቶታል፤ ኢትዮጵያውያን ወይ የራሳችንን ይዘን አልተጓዝን፤ ወይ ምእራባዊያኑን አልሆንን። አጉል ሥልጣኔ የራሳችንን ልብስ እንኳን ከማሳደግ ይልቅ አስጥሎናል፡፡

ፋውንዴሽኑ ሀገር በቀል እውቀት ላይ የተመሠረተ ጥበብ የሚዳብርበትን መንገድ መፍጠር ዓላማው ነው። ለዚህም የሀገር በቀል እውቀትን ይዞ የሚያሳድግ ትምህርት የሚሰጥበት መድረክ ማመቻቸት፤ እንዲሁም፣ በሀገር በቀል እውቀት ዙሪያ የተሻለ የሠሩ ሰዎች የሚሸለሙበትና የሚበረታቱበት መድረክ ለመፍጠር ይሠራል። በቁጭት “አውሮፓ ስለእኛ ትያትር አያውቅም፡፡” የሚለው ጋሽ አያልነህ፣ ለዚህም የእነሼክስፒርን ሥራ ለመሥራት ምእራባዊያኑ ከእኛ የተሻለ መድረክ፣ ተዋናይ እንዲሁም አዘጋጅ ስላላቸው የኛ እነሱን ለመድገም መሞከር ከንቱ ልፋት ነው።

በፋውንዴሽኑ የጥበብ መስኩን ወደ ኢትዮጵያዊነት የሚመልስ ዘርፍ ለማደራጀት እቅድ ተይዟል። ሌላው ዓለም በራሱ የሚያውቀውንና የሰለቸውን የኪነ-ጥበብ ውጤት ከማቅረብ በራሳችን ማንነት ብንቀርብ “ሆ” ብለው ይቀበሉታል የሚለው የፋውንዴሽኑ ሃሳብ ነው። ሀገር በቀል የነበሩት የጥበብ ሙያዎች፣ ሸመና፣ ቀጥቃጭ፣ የሸክላ ሥራ . . . እየተባለ ባለሙያዎቹ እየተናቁና ሌላ ሥም እየተሰጣቸው እንዲተዉት ሲደረግ ቆይቷል የሚለው ጋሽ አያልነህ፤ መድኃኒት፣ ድግምትና መሰል ሀገራዊ እውቀቶች “የጠንቋይ ነው” እየተባለ እንዲጠፉ ተደርጓል። ስለዚህም መሰል ሀገር በቀል እውቀቶችን ለመመለስ ይሠራል፡፡

በምእራባዊያን ዘንድ “አድቬንቸር ፊልም” እየተባሉ በምናብ የሚሠሩት በሀገራችን የነበሩና በማውገዝ የተተውና የተመናመኑ መሆናቸውን ያነሳል። ምእራባውያን እኛን እያስተው እነሱ የኛን በጎን የሚወስዱበትን አሠራር የሚያስቀርና ሀገር በቀል እውቀቶች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን መንገድ መፍጠር ዓላማው አድርጎ፤ ሃሳቡ የገባቸው ሰዎችን ከጎኑ አሰልፎ ለመንቀሳቀስ ፋውንዴሽኑ በሩ ክፍት መሆኑን ይናገራል። የፋውንዴሽኑን ዓላማ ለማሳካት ከመንቀሳቀስ በተጨማሪ፤ ሲገባና ሲወጣ ከከረመበት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሁን ለሦስተኛ ዙር ተመልሶ እያስተማረ ይገኛል። አዕምሮውን ወጣት እንደሆነ ለማቆየት ማንበብና መጻፍ ምርጫው ነው። አካሉን ለማደስ በሳምንት ሦስት ቀን ይዋኛል፡፡

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ለእስራኤል 147 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ የጦር መሣሪያዎችን ለመሸጥ ወሰነች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ዋሽንግተን በኮንግረንሱ ሳታፀድቅ ለቴልአቪቭ አስቸኳይ የጦር መሣሪያ ሽያጭ ስትፈቅድ የሰሞኑ ለሁለተኛ ጊዜ ነው።

አሜሪካ ለእስራኤል 147 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ የታንክ ተተኳሾችን ለመሸጥ ወሰነች። ፔንታጎን "አስቸኳይ" የሽያጭ ውሉን ያፀደቀው የኮንግረንሱን ይሁንታ ሳይጠይቅ ነው።

"ውሳኔው በኮንግረንሱ ለማፀደቅ የሚወስደውን ጊዜ በማሳጠር ለእስራኤል በፍጥነት ለመድረስ ያስችላል" ብለዋል የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን።

ዋሽንግተን ዓለማቀፉን የሰብዓዊ መብት እና የጦርነት ሕግ መሠረት በማድረግ ለአጋሯ ቴልአቪቭ የጦር መሣሪያ ሽያጯን እንደምትቀጥልም መናገራቸውን ሬውተርስ ዘግቧል።

የባይደን አስተዳደር ባለፈው ወርም በተመሳሳይ



ኮንግረንሱን ሳያፀድቅ 45 ሺህ የታንክ ተተኳሾችን ለእስራኤል ለመሸጥ መወሰኑ ይታወሳል።

ይህም ሀገሪቱ እስራኤል በጋዛ በንጹሐን ላይ የምትፈጽመውን ድብደባ እንድትቀንስ ከምታደርገው ጫና ጋር የሚቃረን ነው በሚል ተቃውሞ ሲነሳበት ይደመጣል።

ፔንታጎን በበኩሉ አሜሪካ ለእስራኤል ስለምትሸጠው የጦር መሣሪያ የተቀመጠ ቅድመ ሁኔታ አለመኖሩንና የዋሽንግተንን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ ይቀጥላል በሚለው አቋሙ ጸንቷል።

የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ግን የዋሽንግተን የጦር መሣሪያ ሽያጭ በጋዛ በአየርና በምድር ድብደባዋን ለቀጠለችው እስራኤል ተጨማሪ ኃይል የሚፈጥርና የንጹሐንን ህልፈት የሚጨምር ነው እያሉ ነው።

12ኛ ሳምንቱን በያዘው የእስራኤልና ሃማስ ጦርነት ሕይወታቸው ያለፈ ፍልስጤማውያን ቁጥር 21 ሺህ 507 መድረሱን የጋዛ የጤና ሚኒስቴር አስታውቋል፤ ይህም ከጋዛ ነዋሪዎች 1 በመቶ እንደሚሆን ተነግሯል።

እስራኤል በትናንትናው እለት ብቻ በካን ዩኒስ በፈጸመችው ጥቃት የ200 ፍልስጤማውያን ሕይወት መቀጠፉ ነው የተገለጸው።

## የዓለማችን ቁጥር አንድ ሴት ባለፀጋ ፍራንሶይዝ መየርስ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሙሉ ስማቸው ፍራንሶይዝ ቤትንኮርት መየርስ ይባላሉ፡፡ ፈረንሳዊት ሲሆኑ የሀብት መጠናቸው 90 ቢሊዮን ዶላር እንደደረሰ ብሉምበርግ ዘግቧል፡፡

ዓለም አቀፍ ብራንድ ያላቸው የመዋቢያ እና ፋሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ንግድ የተሠማሩ ሲሆን ይህ ንግድ ከቤተሰባቸው ሲወርድ ሲዋረድ እንደመጣም ተገልጿል፡፡

ለኦሪል የተሰኘ ኩባንያ ወራሽ በመሆን የፋሽን ኢንዱስትሪውን የተቀላቀሉት የ70 ዓመቷ ይህች እንስት አሁን ላይ ቁጥር አንድ የዓለማችን ባለጸጋ እንስት ሆነዋል፡፡

የሁለት ልጆች እናት የሆኑት ፍራንሶይዝ መየርስ በዓለማችን ካሉ አጠቃላይ ቢሊየነሮች ውስጥ በ12ኛ ደረጃ ሲቀመጡ ትርፋቸው በተጠናቀቀው 2023 ዓመት ወደ 35 በመቶ ከፍ ማለቱ ተገልጿል፡፡

በዓመት 524 ቢሊዮን ግብይት የሚፈጸምበት የዓለም ፋሽን ኢንዱስትሪ ከኮሮና ቫይረስ በኋላ ዳግም በመነቃቃት ላይ መሆኑ እንስቷ ተጨማሪ ሀብት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡

ለኦሬል የተሰኘው ይህ ኩባንያቸው በ2023 ዓመት ብቻ የሽያጭ መጠኑ 38 ቢሊዮን ዶላር የደረሰ ሲሆን የአውስትራሊያውን ኤሶፕ ኩባንያንም በ2 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር ጠቅልሎታል፡፡

ለኦሪል የተሰኘው ይህ ፍራንሶይዝ መየርስ ኩባንያ አርማኒ፣ ጂዮርጂዮ፣ ማይቤሊን፣ ሴንት ላውሬንት እና ሌሎችም ብራንዶችን በባለቤትነት ይዟል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍራንሶይዝ መየርስ በመቀጠል አሜሪካውያኑ ጁሊያ ኮች 59 ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም የወልማርት ባለቤቷ አሊስ ዋልተን 56 ቢሊዮን ዶላር ሀብት በመያዝ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ሴት ባለጸጋዎች ናቸው፡፡

ከወንዶች ደግሞ ኢለን መስክ 245 ቢሊዮን ዶላር፣ በርናርድ አርናልት 196 ቢሊዮን ዶላር እንዲሁም ጄፍ ቤዞፍ 168 ቢሊዮን ዶላር ሀብት በመያዝ የዓለማችን ቀዳሚ ባለጸጋዎች ናቸው፡፡



ፍራንሶይዝ ቤትንኮርት


## የጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ ቁጥር 08/2016

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቅ/ጽ/ቤቱ እና በስሩ የሚገኙ መ/ጣቢዎች ተይዞው እና ተወርሰው የሚገኙ አልባሳት የሞተር ሳይክል እና የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፤ልዩ ልዩ እቃዎች፤ ኮስሞትክስ ነክ ዕቃዎች ፤ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፤ሞባይል ቀፎዎች ፤መኪና እና ሎሎች ዕቃዎች በግልጽ እና በሃራጅ ጨረታ ተጫራቾችን አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል::

በዚህ መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የጨረታ ቅድመ ሁኔታዎች እና መስፈርቶች ሚሟላት የሚችሉ ተጫራቾች መወዳደር የሚትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

1. ለጨረታ የቀረቡት ዕቃዎች ላይ ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ተጫራች በጨረታ ከሚሸጠው ዕቃዎች ጋር ተዛማጅነት ያለው የታደሰ የንግድ ፈቃድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርትፍኬት የዘመኑን ግብር የከፈለ ሰለመሆኑ ክሊራንስ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ እንቅስቃሴያቸውን ያሳወቁበት በቅርብ ጊዜ የተሰጣቸው የምስክር ወረቀት እና መለያ ቁጥሩን ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ በኤንቨሎፕ በማሸግ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
2. ተጫራቾች የግልጽ ጨረታ ሰነድ ዘውትር በስራ ሰዓት ከሰኞ እስከ አርብ ከ2፡00-12፡00 ሰዓት እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡00-6፡00 ሰዓት የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) መክፈል በጽ/ቤታችን የእለት ገቢ ገንዘብ ሰብሳቢ ቢሮ ቁር 16 በመገኘት ይህ የጨረታ ማስታወቂያ አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ እስከ መዝጊያው ቀን ድረስ የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
3. በግልፅ ጨረታው ለመሳተፍ ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች የሰጡትን ዋጋ አምስት በመቶ (5%) ዋስትና (CPO) እንዲሁም በሃራጅ ጨረታ የምቀርቡ ዕቃዎችን በተመለከተ 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በጉምሩክ ኮሚሽን በሞያሌ ቅርንጫፍ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስያዝ ይኖርባቸዋል:
4. ጨረታው ሚካሄደው በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት ሲሆን ተጫራቾች (ህጋዊ ወክሎቻቸው) ባሉበት ወይም ታዛቢ ፊት ይከፈታል፡፡
5. ተጫራቾች ማስታወቂያ በጋዜጣው ከታተመበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር እስከ 7ተኛው ቀን ድረስ ለጨረታ የቀረቡ ዕቃዎች ናሙና በሞያሌ እና በሁሉም መ/ጣቢያ የሚገኙ መጋዝኖቻችን እየሄዱ መመልከት አለባቸው::
6. ጨረታው የሚካሄደው ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር በ8ኛው ቀን ሲሆን ጨረታው ከጠዋቱ 3፡45 (ሶስት ሰዓት ከአርባ አምስት ደቅቃ) ተዝግቶ 4፡00 (አራት ሰዓት) ላይ ይከፈታል፤
7. ከላይ በተራ.ቁጥር 6 በተገለጸው ጋዜጣ ከታተመበት ቀን ጀምሮ የምቆጠር 8ኛው ቀን የስራ ቀን ሳይሆን ቢቀር ጨረታው መዝጊያ እና መከፈቻ ቀን በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይሆናል፡፡
8. ለጨረታው አሸናፊ ተጫራቾች ለጨረታው ያስያዙት ሲፒ.ኦ (C.P.O) ከሚከፍሉት ዋጋ ጋር የሚታሰብላቸው ሲሆን ለተሸናፍ ተጫራቾች ደግሞ የጨረታውን ውጤት ከተገለጸ በ 3 ቀናት ውሰጥ ተመላሽ ይደረግላቸዋል:፡
9. አሸናፊ ተጫራች ማሸነፋቸውን በደብዳቤ ወይም በማስታወቂያ ከተገለጸላቸው ቀን ጀምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ያሸነፉበትን ገንዘብ ገቢ በማድረግ ዕቃውን መረከብ ይኖርባቸዋል፡፡
10. ከላይ በተራ ቁጥር 9 በተገለጹት ቀናት ውስጥ ክፍያውን ገቢ ያላደረገ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት CPO ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል፡፡
11 ጽ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ::

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡-** 0464441415 ደውሎ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞያሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኃን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ጥናት ወይስ አስተያየት...!?

በሀገራችን በጣት ከሚቆጠሩ ተጽዕኖ ፈጣሪ አንጋፋ የሙያ ማህበራት ወይም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ግንባር ቀደም ተቋም ነው። ሀገራዊ ፋያዳ ያላቸውን በርካታ ጥናትና ምርምሮችን አካሂዷል። የፖሊሲ ሃሳብ አቅርቧል። ምክረ ሃሳብ ሰጥቷል። የሙሉ ጊዜ ተመራማሪዎች ያሉት፤ የራሱ የሆነ ሕንጻ መገንባት የቻለ ተቋም ነው። የተቋም ሾተላይ በሆነች ሀገር ከአስርት ዓመታት በላይ መዝለቅ በራሱ ስኬት ሆኖ ሊወሰድም ይችላል። ማህበሩ በቅርብ ይፋ ካደረጋቸው ጥናቶች አንዱ በዋጋ ግሽበት ላይ የሠራው ይገኝበታል። ይህ ጥናት በመጽሐፍ ታትሞ ወጥቷል። ሰሞኑን ደግሞ ኢትዮጵያ ብሪክስን በመቀላቀሏ ስለሚኖረው አንድምታ ያደረገውን ጥናት ይፋ ማድረጉን በአማርኛው "ሪፖርተር" ጋዜጣ ላይ ወጥቶ ተመለከትሁ። በጥናቱ ሥነ ዘዴና ግኝት ላይ አንዳንድ ነጥቦችን ለማንሳት ወደድሁ።

ባለፈው ዓመት መጠናቀቂያ ነሐሴ 2015 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ኢትዮጵያ ብሪክስን በይፋ መቀላቀሏ ከተነገረ ጀምሮ ከ330 በላይ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች የተሳተፉበትና ኢትዮጵያ መቀላቀሏ ስላለው ጥቅምና ጉዳት የተደረገውን ጥናት፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ታኅሳስ 11 ቀን 2016 ዓም ይፋ አደረገ፡ ፡ ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ህንድ፣ ቻይናና ደቡብ አፍሪካ የመሠረቱትን ብሪክስ በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም ላይ በይፋ የተቀላቀሉት ኢትዮጵያ፣ ግብፅ፣ ኢራን፣ ሳዑዲ ዓረቢያና የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ መሆናቸው የሚታወስ ሲሆን፣ ማኅበሩ "ኢትዮጵያ ብሪክስን በመቀላቀሏ ምን ትጠቀማለች? ምንስ ትጎዳለች?" የሚለውን ለመለየት ጥናት ማካሄዱን፣ በማኅበሩ የጥናትና ፖሊሲ ትንተና ዳይሬክተር ደግዩ ጎሹ (ዶ/ር) አስረድተዋል፡፡

ማኅበሩ በሠራው የባለሙያዎች ዳሰሳ ጥናት (Expert Survey)፣ ብሪክስን ወይም ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማትን ለማሳተፍ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ ግምገማ መደረጉን፤ በተጨማሪም ማኅበሩ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ዓላማዎቹን ማሳካት አለማሳካቱን በሚመለከት ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን በመጠቀም መገምገሙን፤ ብሪክስ ሰባት ዓላማዎች ያሉት ኒው ዴቨሎፐመንት ባንክ (New Development Bank) ያቋቋመ ሲሆን፣ ዓላማዎቹን የሚያሳካ ከሆነ፣ "ኢትዮጵያ ማሳካት ትችላለች ወይ?" የሚልና ኢትዮጵያ ከሚቀጥለው ወር ጀምሮ አባል መሆኗ (መቀላቀሏ) ሲታወቅ የሚወሰድባት ርምጃ ምን ሊሆን እንደሚችል፣ እንዲሁም ሌሎችንም መለኪያዎች ተጠቅሞ፣ ማኅበሩ ጥናቱን ማካሄዱን ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡

ይሁንና የዳሰሳ ጥናቱ የተለያየ ሙያ ያላቸው ማለትም ከኢኮኖሚክስ በተጨማሪ የዓለምአቀፍ ግንኙነት፣ የሕግ፣ የታሪክና የሌላ ተዛማች ባለሙያዎች ብሪክስን ያዩበትና የተረዱበት፣ እንዲሁም ያላቸው አመለካከት ቢገለጽበት፤ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማለትም የመንግሥት ሰዎች፣ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት፣ የዩኒቨርሲቲ ምሁራንንና ሕዝብ ቢካተቱበት ኖሮ ስለብሪክስ ያለ አተያይን ይበልጥ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ የሚታመን ጥናት ማውጣት ይቻል ነበር። ጥናቱ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎችን ብቻ ማካተቱ ምልኡ እንዳይሆን አድርጎታል ብየ አምናለሁ።

ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከብሔራዊ ጠቅላላ ምርት አኳያ (GDP Per Capita) ባደጉና በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች መካከል ያለው ልዩነት እየጠበበ ነው? ወይስ እየሰፋ ነው?፣ ወደ ውጭ የሚልኩት የንግድ ምጣኔያቸው (FDI) በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት መሻሻል አምጥቷል? የሚሉትን ዓለም አቀፍ መለኪያዎችን በመጠቀም በተደረገው ጥናት፣ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት የገንዘብ ተቋማትን ሪፎርም እንደሚያደርግ ማስታወቁን ጥናቱ ጠቁሞ፣ ነገር ግን የፋይናንስ ጥያቄ በታዳጊ ሀገሮች ቢቀርብም፣ እንደ አሜሪካ የመሳሰሉ ሀገሮች ድጋፍ ካላገኙ በስተቀር ጥያቄያቸው ተቀባይነት እንደማይኖረው ጠቁሟል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በዓለም ባንክም ሆነ በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት (IMF) ከፍተኛ ድምፅ (Voting Power) ያላቸው ሀገሮችን ይሁንታ ስለሚያስፈልግ መሆኑን ማኅበሩ በጥናቱ ማረጋገጡን አስታውቋል፡፡

በእርግጥ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥናት ያስፈልግ ነበር? ወይስ በቀላሉ በደቂቃ ውስጥ በበይነ መረብ አስሶ ማወቅ? በበለጸጉ ሀገራትና በድሃ ሀገራት መካከል ልዩነት እያደገ መምጣት፤ የዓለም ባንክንም ሆነ ዓለምአቀፉን የገንዘብ ተቋም አሜሪካ መር ሥርዓቱ ርዕዮተ አለሙንና ፍላጎቱን በሀገራት ለመጫን የሚጠቀምባቸው ተቋማት መሆናቸው ዓለም ያወቀው፣ ጸሐይ የሞቀው ሀቅ ሆኖ ሳለ ለዚህ ጥናት ገንዘብ፣ ጊዜና ጉልበት መባከን ነበረበት ስል እጠይቃለሁ። ጥናቱ ፓፓው ካቶሊክ ናቸው? ብሎ ከመጠየቅ ጋር ተመሳስሎብኛል። ከዚህ ይልቅ ሌሎች አንገብጋቢ ጉዳዮች መቅደም አልነበረባቸውም። የጥናቱ ሥነ ዘዴስ የባለሙያዎች የዳሰሰ ጥናት ነበር መሆን ያለበት ስል እሞግታለሁ። ምክንያቱም ሙሉ ስዕሉን ማሳየት አይችልም።

የዳሰሳ ጥናቱ ግኝት ተደርጎ ከቀረበው መካከል፤ 37 በመቶ የሚሆነውን ካፒታል ስቶክ የተቆጣጠሩት አምስት ሀገሮች፣ 52 በመቶውን አሥር ሀገሮችና 70 በመቶውን 20 ሀገሮች ድምፅ ያላቸው ሲሆን፣ 162 ሀገሮች ያላቸው ድምፅ 30 በመቶ ብቻ መሆኑን ያትታል። ይሄን ለመውቅስ ጥናት ያስፈልግ ነበር። በተለያዩ የበይነ መረብ የመረጃ ቋት በቀላሉ ማግኘት እየተቻለ። በማስከተልም እነዚህ 30 በመቶ ድምፅ ያላቸው ሀገሮች ለእያንዳንዳቸው ቢካፈል ያላቸው ድምፅ ከአንድ በመቶ በታች ከመሆኑ አንፃር፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትን ሪፎርም ማድረግ የሚለው፣ ዓላማ የተዘነጋና ምንም ዓይነት መሻሻል ያልታየበት መሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል።

የ2ኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ ኃይላት የዓለም ባንክንም ሆነ ዓለምአቀፉን የገንዘብ ተቋም ያቋቋሟቸው ጥቅማቸውን ለማስከበር እንጂ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ አለመሆኑ እየታወቀ ጥናቱ ምን አዲስ ነገር ይዞ መጣ። ከፍተኛ ገቢ ባላቸውና በድሀ ሀገራት መካከል ያለው ልዩነት ትናንትም ዛሬም ነገም የሚቀጥል መሆኑ እየታወቀ ሌላው ይቅርና የአፍሪካ ጥቅል አህጉራዊ ምርት ከጀርመን ያነሰ መሆኑን ለማወቅ በደቂቃዎች በበይነ መረብ ጎልጉሎ ማወቅ እየተቻለ አንጋፋው ማህበር ይሄን ያህል መድከም ለምን አስፈለገው። በጋዜጠኝነት በተሳሳተ ትንተናና ትርጉም ጊዜህንና ጉልበትህን ስታባክን ኤዲተርህ የእንግሊእኛውን ፈሊጣዊ አነጋገር ማለትም "Barking up the wrong tree" ተጠቅሞ በከንቱ ማሰንህ። ደከምህ ሊልህ ይችላል። ይህ ጥናትም ከታላቅ ይቅርታ ጋር በከንቱ የተደከመበት ላብ የፈሰሰበት ነው የሆነብኝ።

ኢትዮጵያ ብሪክስን የተቀላቀለችው ለምንድነው? የሚለውን ጥያቄ 233 የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች አስተያየታቸውን ተጠይቀው፤ ኢትዮጵያ ብሪክስን የተቀላቀለችው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማዕቀብ ጫና ስለበዛባት መሆኑን 49 በመቶ የሚሆኑ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ሲገልጹ፣47 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ አዲስ የኢኮኖሚ ተቋም በመሆኑ እንደሆነ መግለጻቸው ተጠቅሷል፡፡ 41 በመቶ የሚሆኑት ባለሙያዎች ኢትዮጵያ የተቀላቀለችው የውጭ ግንኙነቷ በጣም እየወረደ (እየወደቀ) ስለመጣ በመሆኑ እንደሆነ ሲገልጹ፣ 46 በመቶ የሚሆኑት ባለችበት የጂኦግራፊ አቀማመጥ ምክንያት መሆኑን እንደተናገሩ ደግዩ (ዶ/ር) አስረድተዋል፡፡ 41 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የውጭ ጣልቃ ገብነት ስለበዛባት መሆኑን እንደገለጹና በአጠቃላይ 11 የሚደርሱ ምክያቶችን መስጠታቸውን አክለዋል፡፡

እነዚህ አስተያየት ሰጪ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ተመሳሳይ ሙያ እያላቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ እንዴት እንዲህ አራንባና ቆቦ ወይም የተራራቀና የተለያየ መልስ ሊሰጡ ቻሉ። አሁንም የምለው እነዚህን አስተያየቶች ለመስጠት የግድ የኢኮኖሚክስ ባለሙያ መሆን ይጠይቃል ወይ? ከሆነስ ባለሙያነታቸው ምኑ ላይ ነው የተገለጠው። አዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ወጥተን የሕዝብ አስተያየት ብንጠይቅ ከእነዚህን የተለዩ የአቦሰጥና የአፈተት መልሶችን እናጣለን ወይ የሚል ጥያቄ ያጭርብኛል።

የዚህ ጥናት ሌላው ውስንነት የብሪክስን ጉዳይ ኢኮኖሚያዊ ብቻ አድርጎ ማየቱ ነው። ብሪክስ ከኢኮኖሚ ይልቅ ጂኦፖለቲካዊ ውሳኔ ነው። የድህረ 2ኛውን የዓለም ጦርነት አዲስ የዓለም አሰላለፍ the new world order የመገዳደር ውሳኔ መሆኑን ልብ ይሏል። በዚህ ጥናት 61 በመቶ የሚሆኑት የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ዶላርን ማስወገድ እንደሚቻል፤ 23 በመቶ የሚሆኑት ባለሙያዎች ለማስወገድ አምስት ዓመታትን እንደሚወስድ፣ 53 በመቶ የሚሆኑት ግን አሥር ዓመታት፣ 67 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ 15 ዓመታትን እንደሚወስድና ከዚያም በላይ ዕድሜ እንደሚፈልግ 18 በመቶ የሚሆኑት መግለጻቸውን ደግዩ (ዶ/ር) አብራርተዋል፡፡

ሲጀመር የዓለምን ኢኮኖሚ እንዳሻው ቁጭ ብድግ የሚያደርግ ዶላር እንዲህ በቀላሉ የሚወገድ ምንዛሬ ነውን፤ መልሱን ለባለሙያዎች ልተወው። መልሳቸው አዎ ከሆነ እንዴት የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት እገደዳለሁ። በጥናቱ ሌሎች ግኝቶች ላይ ተመሳሳይ ሙግቶችን ማንሳት ቢቻልም በዚህ ልለፈውና የጥናቱን ምክረ ሀሳብ ላጋራ።ከዚህ በፊት ግን በጥናቱ ላይ ደርዘን ጥያቄዎች እየተነሱበትና የጥናቱ ሥነ ዘዴም በራሱ የሚያከራክር ሆኖ ሳለ ምክረ ሃሳቡስ እንዴት ትክክለኛና ተቀባይነት ያለው ሊሆን ይችላል የሚለውን ያዙልኝ።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር በሰጠው ምክረ ሃሳብ፣ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎቹ መናገር የቻሉት፣ ኢትዮጵያ ብሪክስን የተቀላቀለችው መንግሥት እንደሚለው በሜሪት ወይም ተመራጭ ስለሆነች ሳይሆን ባጋጠማት የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ችግር መሆኑን፤ ብሪክስ ግን ለምን እንደተቀበላት ማንም የሚያውቅ እንደሌለ፣ መስፈርታቸው ህቡዕ መሆኑን፤ ዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ ሥርዓት ዓላማ ስላልተሳካ፣ አዳዲስ የኢኮኖሚ ሥርዓቶችን መፍጠር አስፈላጊ ቢሆንም ጠቃሚነቱን በደንብ ተገምግሞ፣ የኢትዮጵያ መቀላቀልም ከጥቅሙና ከጉዳቱ አንፃር ተጠንቶ መረጋገጥ እንዳለበት፤ ለምሳሌ ያህል ማሌዥያ አመልክታ የነበረ ቢሆንም፣ የሀገሯ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ጥናት አድርገውና ገምግመው ባገኙት ውጤት ‹‹መቀላቀሏ ጥቅም የለውም›› በማለታቸው፣ ሳትቀላቀል መቅረቷን በመጠቆም፣ ኢትዮጵያም ያንን ማድረግ እንዳለባት ምክረ ሃሳቡ ያትታል፡፡

ምርመራው (ግምገማው) ከአባል ሀገሮች ጋር ተነፃፃሪ መሆን ስላለበት፣ ልዩነቱና አንድነቱን መርምሮ፣ የጋራ አጀንዳ ተገምግሞ መሆን እንዳለበት፤ ፈርጀ ብዙ አደጋ ስላለው ኢትዮጵያ እስካሁን ከምዕራቡ ዓለም የምታገኘውን ጥቅም የሚያካክስ ጥቅም መገኘት አለመገኘቱ መረጋገጥ እንዳለበትም፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ባንክና ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ጋር የገባቻቸው ብዙ ስምምነቶች (Engagements) ስላሉ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከብሪክስ ጋር መሥራት የሚያስችላት አለመሆኑን፤ ዋናው የብሪክስ ዓላማና ኢትዮጵያም የተቀላቀለችበት ምክንያት በሀገር ውስጥ ገንዘብ ለመጠቀምና የዶላርን የበላይነት ለመጣል በመሆኑ፣ ይህንን ለማድረግ አዳዲስ አጋር የማግኘት ተግዳሮት ሊገጥማት እንደሚችል ያመላክታል።

ከብሪክስ ጋር በብር መሥራት ከተቻለ፣ ከምዕራባውያን ጋር መሥራት ስለማይቻል ከሁለቱም ተቋማት ጋር መሥራት ግድ ስለሚል፣ በሁለቱም አባል ሀገሮች ተቀባይነትን ማግኘት ግድ ይላል፤ እንደ ህንድ ሩፒ፣ እንደ ቻይና የንና እንደ ሩሲያ ሩብል የኢትዮጵያ ብር ተቀባይነት ያገኝ ይሆን? በሚል የሚጠይቁት የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎቹ፣ ይህ ሁሉ መፈተሽ ስላለበት ጥልቅ ግምገማና ጥናት አስፈላጊ መሆኑን ምክረ ሃሳቡ ይዘክራል።

**እንደ መውጫ**

ጥናቱ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ባህሪያትን፣ ጅኦፖለቲካን፣ ማህበራዊ ባህሪያትን ቢያካትት ኖሮ በተለይ የብሪክስ አባል ሀገራትን ኢኮኖሚያዊ እድገትና ልማት፣ ጥቅል ሀገራዊ ምርት፤ ኢትዮጵያ ከብሪክስ አባላት ጋር ያላት የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት፤ ጂኦፖለቲካዊ አንድምታዎች ማለትም ብሪክስ ከኢትዮጵያና ከአፍሪካ ጋር የሚኖረውን ጂኦፖለቲካዊ አንድምታ፣ ተጽዕኖ፣ ቀጣናዊ መረጋጋትንና ዘርፈ ብዙ ግንኙነቶችን መገምገም፤ የብሪክስ አባል ሀገራት የኢትዮጵያን ልማት ለመደገፍ ያላቸው ቁርጠኝነት፤ ሀገራችን ከአባላቱ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ያላት ግንኙነት፤ ወዘተረፈ በጥናቱ ቢዳሰሱ ኖሮ ጥናቱ ሙሉ ስዕልን የማሳየት ጉልበት ይኖረው ነበር። ማህበሩ ከዚህ አንጻር ጥናቱን መለስ ብሎ ይፈትሸዋል የሚል እምነት አለኝ።

ሻሎም !

አሜን።

# ስፖርት





## ታሪካዊው የሴካፋ ዋንጫና የኢትዮጵያ ድል

**ቦጋለ አበበ**

ታህሳስ 17 ቀን 1980 ዓ.ም በኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ ልዩ ቀን ሆና ትታወሳለች። ከዛሬ 36 ዓመት በፊት ልክ በዛሬዋ ዕለት ኢትዮጵያ ባዘጋጀችው የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪቃ የእግር ኳስ ዋንጫ (ሴካፋ) ዚምባብዌን በፍጹም ቅጣት ምት በማሸነፍ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ዋንጫውን ከፍ ያደረገችበት ዕለት ነበር።

ይህች ልዩ ቀን በተለይም የፍፃሜውን ጨዋታ በቀጥታ ሲያስተላልፍ በነበረው አንጋፋው የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ዛሬም ድረስ ትታወሳለች። « ... ወይኔ! ወይኔ! ወይኔ ገብሬ! ገብሬ የመታውን የዚምባብዌው 2 ቁጥር በራሱ ግብ ላይ ... በራሱ ግብ ላይ ከመረብ አሳረፈ ... በራሱ ግብ ላይ ከመረብ አሳረፈ ...

ዋንጫውን ለብሔራዊ ቡድኑ አምበልና ለአሁኑ የዋልያዎቹ አሠልጣኝ ገብረመድኅን ኃይሌ የሰጡት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢሕዴሪ) ፕሬዚዳንት፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም ሲሆኑ፣ የተሰማቸውን ደስታ የገለጹት 100 ሺ ተመልካች የሚይዝ ስታዲየም ለመሥራት ቃል በመግባት ነበር።

በ1980 ኢትዮጵያ ያስተናገደችው ይህ የሴካፋ ውድድር በብዙ ነገሮች ተወጥራ የነበረችውን ሀገር በአንድነት ያቆመ እንደነበር ይነገራል። ኢትዮጵያ ከብቸኛው የአፍሪካ ዋንጫ ድሏ 26 ዓመታት በኋላ ያነሳችው የመጀመሪያ የሴካፋ ዋንጫ በወቅቱ ወግ አጥባቂ ሶሻሊስቶች ሳይቀሩ ያወጁትን ሰዓት እላፊ ረስተው በደስታ የዘለሉበት ነበር።

ውድድሩ በሁለት ምድብ ተከፍሎ የተካሄደ ሲሆን ኢትዮጵያ ከኬንያ ፣ ታንዛንያ እና ዛንዚባር ጋር በምድብ አንድ ተደልድላ ጨዋታዎቿን በአዲስ አበባ አድርጋለች። በአመዛኙ አዲስ ትውልድ ይዛ የቀረበችው ኢትዮጵያ የመክፈቻ ጨዋታዋን ከታንዛንያ ጋር አድርጋ ባዶ ለባዶ አጠናቀቀች። በሁለተኛ ጨዋታም በተመሳሳይ ከዛንዚባር ጋር በተመሳሳይ ያለ ጎል ተለያይታ ከብዙዎች የዋንጫ ግምት ውጭ ሆነች። ሆኖም በሦስተኛው ጨዋታ ጠንካራዋ ኬንያን ሁለት ለአንድ በማሸነፍ በአምስት ነጥብ በግብ ክፍያ ተበልጣ ዛንዚባርን ተከትላ ወደ ቀጣይ ዙር አለፈች።

በመቀጠል በግማሽ ፍፃሜው የወቅቱ ስመ ገናና ቡድን ዛምቢያን አራት ለባዶ አሸንፋ የመጣችው የውድድሩ ቁንጮ ዩጋንዳን ሦስት ለባዶ በመርታት ወደ ፍፃሜ አለፈች። በፍፃሜው ጨዋታም ዚምባብዌን ገጥማ እስከ ተጨማሪ ደቂቃ ስትመራ ብትቆይም የወቅቱ ድንቅ አጥቂ ገብረመድኅን ኃይሌ በመጨረሻዎቹ ሽርፍራፊ ደቂቃዎች ባስቆጠራት ግብ መደበኛው የጨዋታ ክፍለ ጊዜ በአቻ ውጤት ተጠናቀቀ። ጨዋታው በተጨማሪ ደቂቃዎች ቀጥሎ ሁለቱም ቡድኖች ግብ ባለማስቆጠራቸው ወደ መለያ ምት አምርተው ጨዋታው በድራማዊ ትዕይንቶች ታጅቦ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተጠናቀቀ።

በውድድሩ ድባብ እና ጨዋታውን በቴሌቪዥን ሲያስተላልፍ የነበረው ደምሴ ዳምጤ የሚታወሱ ገለፃዎች አሁንም ድረስ ከኢትዮጵያውያን አዕምሮ ስላልወጣው ውድድር የወቅቱ የቡድኑ አምበል የነበረው እና ወሳኟን የፍፃሜ ግብ ያስቆጠረው እንዲሁም ውድድሩን በተጫዋችነት እና ኋላ ላይ ደግሞ በረዳት አሰልጣኝነት



**ኢትዮጵያ ከአፍሪካ ዋንጫ በኋላ ያገኘችው ታሪካዊ የሴካፋ ድል 36 ዓመት ሞላው፣**

ያሸነፈው ገብረመድኅን ኃይሌ ትውስታውን በተለያዩ አጋጣሚዎች ገልጿል።

ገብሬ በአንድ ወቅት ከሶከር ኢትዮጵያ ጋር ባደረገው ቃለምልልስ እንዲህ በማለት ነበር ትውስታውን ያጋራው፤

“ ወቅቱ ትልቅ ሀገራዊ አንድነት ያስገኘ ውድድር ነበር፤ ቡድናችን ሁለት ተከታታይ ጨዋታዎች አቻ ተለያይቶ ነበር ውድድሩን የጀመረው። ሴካፋ ዋንጫ እንደ አሁኑ የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን ብቻ ሳይሆን የመካከለኛ እና ደቡብ አፍሪካ ሀገራትን ያካተተ ጠንካራ ፉክክር የሚደረግበት ነበር። በውድድሩ ጅማሮ ነጥቦች ጥለን ነበር፤ ከዛ ግን ተከታታይ ጨዋታዎች አሸንፈን ወደ ጥሩ መንፈስ የመጣንበት ውድድር ነበር።

“የፍፃሜው ጨዋታ ብዙ ድራማዎች ነበሩት። አንዱ በጨዋታው የነበረው እንቅስቃሴ፣ የደጋፊያችን ጉጉት እና በጨዋታ መሐል የነበረው ተጫዋቾቻችን ጉዳት እና ድካም ነበር። ብዙ ተሰላፊዎቻችን ደክመው መጠነኛ ጉዳታቸውን ተቋቁመው ነበር ጨዋታውን ያካሄዱት። ሌላው የማልረሳው ደግሞ ጎሏ የገባችበት መንገድ እና ደቂቃው ነው። ከመስመር የተሻማችው ኳስ በግምባር ለማስቆጠር ከሚያዳግት ቦታ ነበር ገጭቼ ያስቆጠርኳት። ሌላው ደቂቃው ነው፤ መደበኛ ሰዓት ተጠናቆ የተሰጠው ተጨማሪ ደቂቃ ሊያልቅ ሽርፍራፊ ደቂቃዎች ሲቀሩት ነበር ጎሉን አግብቼ አቻ የሆንነው። እንደውም ግቡ ካስቆጠርን በኋላ ደስታችን ገልፀን ልክ እንደገባን ነው የጨዋታው ማጠናቀቂያው ፊሽካ የተነፋው።

“በጣም የሚገርመው እና አጓጊ የነበረው ደግሞ የመለያ ምቱ ድራማ ነው። እኔ፣ ነጋሽ ተክሊት እና አማኑኤል ኢያሱ በተከታታይ መለያ ምቶቹን አስቆጠርንና እነሱ አንድ አስቆጥረው፤ ተካበ ሁለት መልሶ ሦስት ለአንድ መራን። ከዛ ቀጥሎ በቀለ ብርሃኑ ሳተ፤ በድጋሚ ዕድል ተሰጥቶትም ሳተውና እነሱ አገቡ። ከዛ በኋላ የነበረው አምስተኛ መቺው መንግሥቱ ሁሴን ቢያገባው እናሸንፍ ነበር፤ ሆኖም ሳተና ሦስት አቻ ሆን ውጥረት ውስጥ ገባን። ከዛ ግን ወደ ተጨማሪ ምት ተሸጋግረን የዚምባብዌ መቺ ሳተና እኛ በዳኛቸው ደምሴ አማካኝነት አስቆጥረን ጨዋታውን አሸነፍን።

“ከጨዋታው በኋላ የነበረው ደስታ ልዩ ነበር። የህዝቡ ስሜት በቃላት ለመግለፅ ይከብዳል። ጨዋታው ልክ እንደተጠናቀቀ ሕዝቡ ደስታውን መቆጣጠር አቅቶት ሜዳ ውስጥም ገብቶ ነበር። በዛን ወቅት የሰዓት እላፊ ነበር። ዋንጫውን ካነሳን በኋላ ግን በደስታ ብዛት ለቀናት የሰዓት እላፊው ተነስቶ ነበር። ሀገራዊ አንድነት እና ጥሩ የእግር ኳስ መነሳሳት የነበረበት ወቅት ነው። ”




## ሀገር ወዳዱ ቃለአብ

**እየሩስ ተስፋዬ**

እንዴት ናችሁ ልጆችዬ? ሁሉ ሠላም ነው? ሳምንቱ እንዴት አለፈ? መቼም በትምህርት፣ በጥናት፣ ወላጆቻችሁን በማገዝ፣ የተለያዩ መጻሕፍትን በማንበብ እንዳሳለፋችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ልጆችዬ፣ ከትምህርታችሁ ጎን ለጎን ማድረግ የሚያስደስታችሁ ነገር ምንድ ነው? የፈጠራ ሥራዎችን መሥራት፣ ሥዕል መሳል፣ ሙዚቃ እና የሙዚቃ መሣሪያዎችን መጫወት እና ሌሎችንም እንደምትዘረዝሩልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ልጆችዬ፣ ዛሬ አንድ ጎበዝ ታዳጊ ገጣሚ ልናስተዋውቃችሁ ነው። በትምህርቱም ደግሞ ጎበዝ ነው። “ማነው?” አላችሁ አይደል? እንግዲያውስ እናስተዋውቃችሁ

ቃለአብ ሸዋፈራው ይባላል። የአንጋፋው አርቲስት ደበበ እሸቱ የልጅ ልጅ ነው። በቅዱስ ዮሴፍ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ነው። ልጆችዬ፣ ቃለአብ በትምህርቱ ጎበዝ ሲሆን፤ ከአንድ እስከ አምስተኛ የሚወጣ የደረጃ ተማሪ ነው። ከትምህርቱ ጎን ለጎን የተለያዩ ግጥሞችን ይጽፋል። መፃፍ ብቻ እንዳይመስላችሁ፤ በተለያዩ መድረኮች ላይ በመጋበዝ ግጥሞቹን ያቀርባል። ለምን አንድ ግጥሙን አናስነብባችሁም? የግጥሙ ርዕስ ‹‹አንቺ›› ይሰኛል።

አንቺ
የሰው ዘር መገኛ፣ የአዳም ፍጥረት ቤቱ
ለበኩር ለቃኤል የእድገት መሠረቱ
ለታናሽ ለአቤል ለመኖር ምክንያቱ
አንቺ የሥልጣኔ ምንጭ ታሪክ የማበርከት
በነዛግዌ መንደር በአክሱም ነገሥታት
የጀብድ ሁሉ አዋጅ የታሪክ መሠረት




**ታዳጊ ቃለአብ ሸዋፈራው**

በዮሐንስ ዘመን በምኒልክ መንግሥት
አንቺ፣ አንቺ ማለት እኮ፣ የድህነት መስኮት
አንቺ ማለት እኮ የሰው ልጆች አጥንት
አንቺ፣ አንቺ፣ አንቺ፣ አንቺ ማለት እኮ
ለድንበርሽ ክብር ደም የተራጩልሽ
የጀግናን ማንነት ባንቺ ያሳዩብሽ
ለአምላክ ሊነግሩልሽ
ዝቅ ብለው ወደታች መሬት የሳሙልሽ
አንቺ ማለት እኮ የዓለም ንግሥት ነሽ
ታዲያ፣ ታዲያ ለዚህ ክብርሽ
ለአንቺ የሚመጥን ስያሜ ባጣልሽ
በሙሉ አንደበቴ ኢትዮጵያ ልበልሽ።

ልጆችዬ፣ አነበባችሁት? ቃለአብ ጎበዝ ገጣሚ ነው አይደል? ሀገሩንም በጥሩ ግጥም እንደገለፃት ተረድታችኋል ብዬ አምናለሁ። ቃለአብ ለወደፊት የምህንድስና ባለሙያ (አርክቴክት) የመሆን ፍላጎት አለው። እንዲሁም፣ በሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ትልቅ አሻራ የማሳረፍ ዓላማም አለው። ዓላማውን እንዲያሳካ እና ግጥሞቹን እንዲፅፍ አንጋፋው አርቲስት ጋሽ ደበበ እሸቱ ያበረታቱታል። እርሱም አያቱ ስለሚያበረታቱት ደስ ይለዋል። ሌሎች ግጥሞችን በማንበብ ልምድ መውሰዱንም ይናገራል። እናቱ ወይዘሮ ዮዲት ደበበም ርዕሶችን በማስተካከል፣ ምክር እና ሃሳብ በመስጠት እገዛ ታደርግለታለች፤ ታበረታታዋለችም።

የ14 ዓመቱ ታዳጊ ቃልአብ ግጥም መፃፍ የጀመረው ፈልጎ ወይም አቅዶ አይደለም። እንደ ድንገት ወይም እሱ እንደሚለው እንደ ዕድል መፃፍ የጀመረ ሲሆን፤ ልጆች ዝንባሌያቸውን እና ተሰጥኦዋቸውን እንዲያወጡ ወላጆች ማገዝ እንዳለባቸው ይገልፃል። ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ መሞከር እና እስከ መጨረሻው ድረስ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው፤ እንዲሁም፣ ተስፋ መቁረጥ እንደሌለባቸው ይመክራል።

ልጆችዬ፣ በትምህርት ቤታችሁ ብዙ ክበባት እንዳሉ ይታወቃል። ታዲያ እናንተ በየትኛዎቹ ክበባት ትሳተፋላችሁ? የቃለአብ እንንገራችሁ። እሱ በብዙ ክበባት ውስጥ ይሳተፋል። በተለይም በሚኒሚዲያ ክበብ በመሳተፍ ግጥሞቹን ያቀርባል። እናም ልጆችዬ፣ ግጥሞቹን በሚኒሚዲያ ላይ በማቅረቡ ዛሬ ላይ ትልልቅ መድረኮች ላይ ተገኝቶ ግጥሞቹን እንዲያቀርብ ብቻ ሳይሆን በራስ የመተማመን አቅሙንም ጨምሮለታል።

በልጆች ዓይን ሁሉም ነገር ጥሩ፣ መልካም እና ንጽህ እንደሆነ ነው ቃለአብ የሚናገረው። ስለዚህም ይህንን በመረዳ ወላጆች ልጆቻቸውን ኮትኩተው ቢያሳድጉ፣ ድጋፍ ቢያደርጉላቸው እና ራሳቸው (ልጆቻቸው) በሚፈልጉበት መንገድ እንዲሄዱ ቢያግዟቸው የነገ ሕይወታቸው ስኬታማ እንዲሆን ያግዛል። ከድሮ ነገሥታቶች አፄ ምኒልክ፣ አፄ ኃይለሥላሴ፣ አፄ ዮሐንስ እና አፄ ቴዎድሮስን አብዝቶ ይወዳቸዋል። የመውደዱ ምክንያት ደግሞ ኢትዮጵያ አሁን ለደረሰችበት ዕድገት የእነርሱ ትልቅ ዐሻራ ማሳረፍ እንደሆነ ይጠቅሳል።

ልጆች ከቃለአብ ዕድሜ ከፍ ያሉትም ይሁኑ ታናናሾቹ አብዛኞቹ ልጆች ስልክ፣ ታብሌት እና መሰል ነገሮችን አብዝተው ይጠቀማሉ። እርሱ ግን ለአስፈላጊ ነገር ብቻ ነው የሚጠቀመው። የእሱ እናት እና አባት መልካም ወላጆች ናቸውና አልባሌ ነገር ላይ ጊዜውን እንዲያጠፋ አያደርጉትም።

ብዙ ልጆች ስልክ እና የመሳሰሉትን ከመጠቀም ባለፈ ሱሰኛ እንደሆኑ ታዝቧል። ለዚህ ደግሞ የወላጆች ሚና ቀላል የሚባል አይደለም ይላል። ለእዚህ ልጆች ቃለአብ የሚመክራቸው ነገር አለ። ወላጆች ልጆቻቸውን በጥሩ ይሁን በመጥፎ መንገድ የመቅረጽ አቅም አላቸውና ቤተሰብ ላይ መሥራት እንደሚያስፈልግ ይናገራል። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ትኩረታቸው ትምህርት ላይ ብቻ መሆን አለበትም ይላል።

ታዳጊው ቃለአብ ዛሬ በተለያዩ መድረኮች ላይ ተጋብዞ ግጥም እንዲያቀርብ ላገዙት እና ላበረታቱት ለአያቱ ለአርቲስት ጋሽ ደበበ እሸቱ፣ ለእናቱ፣ ለአባቱ እና ለጓደኞቹ፤ እንዲሁም፣ ድጋፍ ለሚያደርጉለት ሁሉ ምስጋውን አቅርቧል። ልጆችዬ፣ ከታዳጊው ልጅ ብዙ ነገር እንደተማራችሁ እተማመናለሁ። በሉ ልጆችዬ፣ ሳምንት በድጋሚ ለመገናኘት ያብቃን።